# አዲስ ዘመን

እንድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 296 ሰኔ 26 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







ፎቶ፡- በገባቦ ገብሬ

## ‹‹ታሪካችንን የማይመጥኑ እኩይ ድርጊቶችን እያወገዝን በዓለም ተወዳዳሪና የምንኮራባት ኢትዮጵያን መገንባት የእኛ ኃላፊነት ነው››

- አቶ ደመቀ መኮንን
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ታሪካችንን የማይመጥኑ እኩይ ድርጊቶችን እያወገዝን በዓለም ተወዳዳሪና የምንኮራባት ኢትዮጵያን መገንባት የእኛ ኃላፊነት ነው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ለ8ኛ ዙር ያስተማራቸውን አንድ ሺ 474 ተማሪዎችን አስመርቋል፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ትናንት በተካሄደው የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ እንደገለጹት፤ አገራችንን የምናስከብረው፣ የምናበለጽገው፣ በአንድነት፣ በመደጋገፍና በመከባበር

‹‹ታሪካችንን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሲቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደሰ

## ጉባኤው ሕግ የማስከበር ተግባሩ እንዲጠናከር አሳሰበ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ሙሉ በሙሉ ፊቱን ሰላም ማስፈን፣ የሕዝብን ደሕንነት ማስጠበቅና ሕግ ማስከበር ላይ ማተኮር አለበት ሲል የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አሳሰበ፡፡ የአባቶች እና የሃይማኖት ተቋማትን ምክር አለመስማት ፍጻሜው ጥፋት እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባልም ብሏል፡፡

ጉባኤው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “ሕወሓት መንግሥት የሰጠውን የሰላም ዕድል ቢጠቀም የትግራይ ሕዝብ ስቃይ ያጥራል”

- አቶ ሙሉብርሃን ሃይሌ
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /ትዴፓ/ የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት መንግሥት የሰጠውን የሰላም ዕድል ቢጠቀም የትግራይን ሕዝብ ወደ ከፋ ችግር እንዳይገባና ስቃዩም እንዲያጥር ያደርጋል ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /ትዴፓ/ የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ ገለጹ፡፡

ሃላፊው አቶ ሙሉብርሃን ሃይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ለሰላም ሁሌም ቁርጠኛ አቋም አለው፡፡ ከጦርነቱ በፊትም መንግሥት ችግሮች በውይይትና በሰላማዊ መልኩ እንዲፈቱ ብዙ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ ወደ ጦርነት ላለመግባት ብሎ መንግሥት እያየ እንደአላየ ያላፋቸው በርካታ ችግሮች ቢኖሩም አሸባሪው ሕወሓት የሰላም አማራጭ አልፈልግም ብሎ ጦርነት ከፍቶ የትግራይን ሕዝብ ለከፋ ችግርና ለስቃይ ዳርጓል፡፡ አሁንም አሸባሪው ሕወሓት መንግሥት የሰጠውን የሰላም ዕድል ቢጠቀም የትግራይን ሕዝብ ወደ ከፋ ችግር እንዳይገባና ስቃዩም እንዲያጥር ያደርጋል፡፡

አገር የሚገነባውና ችግሮች የሚፈቱት በድርድርና በሰላማዊ መንገድን በመከተል ነው ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የሕወሓት ቡድን ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በድርድር ቢፈታ የትግራይ ሕዝብ እያጋጠመ ካለው ስቃይና መከራ እፎይታ ያገኛል ብለዋል፡፡

የሕወሓት ቡድን በሰላም የሚያምን ድርጅት ቢሆን ኖሮ ሃላፊነት በጎደለው መልኩ አገራችን ኢትዮጵያ ወደ ግጭት እንድትገባ አያደርግም ነበር ያሉት ሃላፊው፤ የትግራይ ሕዝብም የችግር ገፈት ቀማሽ አይሆንም ነበር ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሙሉብርሃን ገለጻ፤ ቀደም ሲል የተደረገው ጦርነት አስፈላጊ አልነበረም፤ ምክንያቱም በጦርነት የሚፈታ ችግር የለምና፤ የሕወሓት ቡድን አሁንም መንግሥት የሰጠውን የሰላም ዕድል በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል፡፡

ሰላም በአንድ ወገን ብቻ የሚፈለግ ከሆነ ትርጉም አይኖረውም የሚሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ውይይቱ ውጤታማ እንዲሆን የትግራይ ሕዝብ አሸባሪውን ሕወሓት ማስገደድና ጫና መፍጠር አለበት፤ ምክንያቱም የጦርነቱ ገፈት ቀማሽ የትግራይ ሕዝብ ነውና ብለዋል፡፡

‹‹ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

## ኢትዮጵያን በውክልና ጦርነት ለማዳከም የሚፈልጉ ሃይሎችን ሴራ ሕዝቡ ሊገነዘበው እንደሚገባ ተገለጸ

ገጽ 4







# የተለያዩ ዩኒቨርሲዎች ተማሪዎቻቸውን አስመረቁ


በጋዜጣው ሪፖርተሮች

አዲስ አበባ፡- የተለያዩ  የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች ያስተማሯቸውን ተማሪዎቻቸውን አስመረቁ።

ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ አምቦ ዩኒቨርሲቲ፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ በትናንትናው ዕለት ተማሪዎቻቸውን አስመርቀዋል።

የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ በተለያየ የትምህርት መርሃ ግብር ያሰለጠናቸውን ከስድስት ሺህ በላይ ተመራቂዎችን በመጀመሪያ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ ለ23ኛ ጊዜ ትናንትና ሲያስመርቅ የኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር መኩሪያ ኃይሌ በክብር እንግድነት ተገኝተዋል።

በተመሳሳይ የጅማ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ የትምህርት መስኮች በመጀመሪያ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ እንዲሁም በስፔሻሊቲ እና ሰብ ስፔሻሊቲ ያስተማራቸውን  ሁለት ሺህ 509 ተማሪዎች አስመርቋል ።


ፎቶ፡ በፀሐይ ንጉሴ

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጀማል አባፊጣ  በምረቃው ሥነ ስርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ምሩቃን ለሕዝብ ሰፊ ጥቅም የሚሰጡ እንደ ህዳሴው ግድብ፣  በምግብ ራስን የመቻል ጥረቶች፤ አረንጓዴ አሻራ፣ ግብርናና የተፈጥሮ ሀብት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

በተጨማሪም የቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግ እንዲሁም የዴሞክራሲን ባህል ለማዳበር እየታዩ ያሉ ጅምሮችን አጠናክሮ በማስቀጠል ለሀገር ዕድገት  የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል ብለዋል፡፡

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲም በ35ኛ ዙር የምረቃ መርሃ ግብሩ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ከመጀመሪያ እስከ ሶስተኛ ዲግሪ ያሰለጠናቸውን ሁለት ሺ 561 ተማሪዎችን አስመርቋል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳምጠው ዳርዛ፤ ጊዜንና ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም በትጋት ከሰራን የሀገራችንን ዕድገትና ክብር ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ እንችላለን ሲሉ በወቅቱ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲም በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም በሶስተኛ ዲግሪ በተለያዩ መርሀ ግብሮች ሲያሰለጥናቸው የቆየውን ሁለት ሺህ 683 ተማሪዎች አስመርቋል። በወቅቱ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ፤ ተመራቂዎች በዩኒቨርሲቲው የቀሰሙትን ዕውቀት ከወትሮው በተሻለ ሀገራዊ ለውጥና ዕድገት እንዲያውሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በተመሳሳይ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በህክምና ዶክትሬት ዲግሪ፣ በስፔሻሊቲና ሰብ-ስፔሻሊቲ ፕሮግራሞች ያስተማራቸውን 334 ሐኪሞችን ትናንትና አስመርቋል። የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር አስራት አፀደወይን ተመራቂዎች ባለፉት ዓመታት የደረሱ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የሰው ልጅ ስቃዮችን በማከም፣ በፍጹም ፍቅርና እንክብካቤ የሕዝብ አገልግሎታቸውን የጀመሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

አምቦ ዩኒቨርሲቲም በተለያዩ መስኮች ያስተ ማራቸውን ከአራት ሺህ 400 በላይ ተማሪዎችን አስመር ቋል። በወቅቱ በክብር እንግድነት የተገኙት የማዕድን ሚኒስትር ኢንጅነር ታከለ ተመራቂዎች ባስተላለፉት መልዕክት አይናችሁን ለደቂቃም ቢሆን ከአላማችሁ ላይ አታንሱ። ለፈተና ሳትበገሩ፣ ለግራና ቀኝ ጩኸቶች ሳትዘናጉ መንገዳችሁን ቀጥሉ፣ ያኔ ኢትዮጵያ ላለመችለት ፅኑ አላማ መቆማችሁን በተግባር ታረጋግጣላችሁ ብለዋል።

በተጨማሪ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ በተለያዩ የሙያ መስኮች ያስተማራቸውን 1ሺህ 510 ተማሪዎች አስመርቋል። በምረቃ ስነ-ስርዓቱ የኢፌዴሪ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትር ዴኤታ እና የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ብርሃኑ መገርሳ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በበኩሉ ለ10ኛ ጊዜ አንድ ሺህ 495 ተማሪዎችን ሲያስመርቅ፤ በተመሳሳይ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ያሰለጠናቸውን አንድ  ሺህ 320 ተማሪዎችን በመጀመሪያ፣ሁለተኛ፣በሶስተኛ ዲግሪ አስመርቋል።

በሌላ በኩል የቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ከዲፕሎማ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ በተለያየ የትምህርት ዘርፍ ያስተማራቸውን ተማሪዎች አስመርቋል።



# ለራስ ቴአትር ቤት ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ተቀመጠ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለራስ ቴአትር ቤት ግንባታ የመሰረት ድንጋይ አስቀመጡ፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የራስ ቴአትር ቤት ግንባታ መጀመሩ መስተዳድሩ ለኪነጥበቡ ዘርፍ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል።

ለኪነጥበቡ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራን መሆኑን የሚያሳዩ ተጨማሪ ማስረጃዎች አሉ።  በከተማችን 10 አምፊ ቴአትሮችን በማስገንባት የማዘጋጀ ቤቱ የባህል አዳራሽ ባማረ መልኩ የገነባን ሲሆን፤ አሁንም የመጀመሪያውን አዲስ ቴአትር ቤት ግንባታ የመሰረት ድንጋይ አስቀምጠናል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ባህልና ቴአትር ቤት ግንባታ እንዲሁም ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ሕፃናትና ወጣቶችን ቴአትርና ሀገር ፍቅር ቴአትር ቤቶችን ግንባታ እየተጠናቀቁ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የማንጨርሰውን አንጀምርም ፤ ይህንንም የራስ ቴአትር ቤት ግንባታ አስጀምረን እንጨርሳለን ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ጥበብ ትውልድን በመቅረፅና በመገንባት ትልቅ ሚና ስላላት አሁንም ትኩረት ሰጥተን መስራታችንን እንቀጥላለን ሲሉ አስታውቀዋል።

እኛ በየዘርፋችን ጠንክረን ስንሰራ አገራችን ታድጋለች፤ ሙያተኞችም ጥበባችሁን ተጠቅማችሁ በሀገር ግንባታ በተለይም በሰላምና ፀጥታ ማረጋገጥ ላይ በርትታችሁ ስሩ በማለት መልዕክት ማስተላለፋቸውን ከከንቲባ ፅህፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በኢትዮጵያ የጥበብ ጉዞ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው በርካታ አንጋፋ አርቲስቶችን ለሀገር ያበረከተው የራስ ቴአትር ቤት አዲስ ግንባታ ማስጀመሪያ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ ከከንቲባ አዳነች አቤቤ በተጨማሪ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሒሩት ካሳው እንዲሁም አንጋፋ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

# ሁለተኛው “ክብር ለጥበባት” ሀገር አቀፍ የዕውቅና መድረክ ሰኔ 29 እንደሚካሄድ ተገለጸ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- ሁለተኛው "ክብር ለጥበባት" የተሰኘው ሀገር አቀፍ የዕውቅና መድረክ ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም እንደሚካሄድ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ሚኒስቴሩ መርሃ ግብሩን ከጥበብ ሙያ ማሕበራት ጋር በመተባበር እንደሚያዘጋጀው ተገልጿል፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ዴኤታ ወይዘሮ ነፊሳ አልመሃዲ መርሃ ግብሩን ው ለጋዜጠኞች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ አንጋፋ የጥበብ ሙያተኞች ህያው ሆነው በስራቸው እንዲዘከሩ ለማድረግ የዕውቅና ሥነሥርዓቱ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በሚካሄደው መድረክ በአስር የጥበብ ዘርፎች ለ45 ጥበበኞች ዕውቅና ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ጠቁመው፤ ዕውቅናው ከአንጋፋ የጥበብ ሙያተኞች አርዓያነት በመውሰድ በሙያው ሥነ ምግባር የታነጸ ጠንካራ ተተኪ ለማፍራት እንደሚረዳ ገልጸዋል።


ፎቶ፡ በፀሐይ ንጉሴ

ወይዘሮ ነፊሳ አልመሃዲ

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሀገር አቀፍ የጥበባት ሽልማት ኮሚቴ በመመሪያ እንዲቋቋም ማድረጉንም አስታውሰው፤ ሚኒስቴሩ ዘርፉን ለማጠናከር የሚረዳውን የዕውቅና መድረክ ግልጽ በሆነ ሂደት እንደሚመራ ጠቁመዋል።

መስፈርቱን የሚያሟሉ በዘርፉ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በዕድሜ ልዩነት ሳይደረግባቸው ዕውቅና እንደሚሰጥ ገልጸው፤ ሁሉም ተሸላሚ በሕይወት ዘመን ተሞክሮውና በትውልዱ ላይ ያመጣውን ለውጥ መሰረት ያደረገ የማሟሪያ መድረክም እንደሚፈጠር ተናግረዋል።

ለጥበብ ሙያተኞች ክብርና ድጋፍ መስጠት የሀገር የኪነጥበብና የባህል ኢንዱስትሪ በማሳደግ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ተመሳሳይ የዕውቅና መድረኮችን እያጎለበቱ መሄድ ይገባል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ጥበብ በአንድ ሀገር ማሕበራዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮችን በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ አለው። ዜጎች ለልማት በማነሳሳት ልምዶችና ዕውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የሚያግዝ በመሆኑ መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማሕበር ፕሬዚዳንትና የዕውቅና አሰጣጥ ምልመላና መረጣ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዳዊት ይፍሩ በበኩሉ፤ በሙያው ረጅም ዓመታት ያሳለፉ፣ በስራቸው ትጋትና ውጤታማነት የሚታወቁ፣ ፣ተተኪ ለማፍራት ሰፊ ጥረት ያደረጉ የጥበብ ባለሙያዎች ዕውቅና እንደሚሰጣቸው ገልጿል።

ሙያቸውን በመጠቀም ሀገራዊ እሴቶችን በማስተዋወቅ ረገድ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙና በስነምግባራቸውም ለሌሎች ዓርዓያ የሚ ሆኑ ተመልምለው ዕውቅና እንደሚሰጣቸውም አስታውቀዋል።

በሥነ-ጽሑፍ፣ በሙዚቃ ጥበብ፣ በውዝዋዜ፣ በሰርከስ፣ በቴአትር፣ በሲኒማ፣ በመዝናኛ፣ ፋሽንና ፣ዕደጥበብ ዲዛይን ፣ በሥዕልና በዲጂ የሙያ ዘርፎች ዕውቅና እንደሚሰጥ ታውቋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስለሰላም የሚከፈለውን ሁሉ በመክፈል ነገዎቻችንን ብሩህ እናድርግ!

ሰላም ከፍ ያለ ዋጋ ያለው፤ የሚያስከፍለውም ዋጋ በቀላሉ የማይሰላ ትልቅ ማህበረሰባዊ እሴትም ነው። የነገዎች መገኛ፤ የማህበረሰብ ሁለንተናዊ ተስፋ ማሰሪያ ገመድ ነው። በብዙ መልኩ ጦርነት ከሚጠይቀው ዋጋ በላይ ሊያስከፍል የሚችል፤ ለዚህም በሁለንተናዊ መልኩ እራስን ማዘጋጀት የሚጠይ ነው።

በቀደሙት ዘመናት ሆነ ዛሬም ዓለም ለሰላም ከከፈላቸው ዋጋዎች ይልቅ ለጦርነቶች ከፍ ያለ ዋጋ ለመክፈል የተገደደባቸው እውነታዎች እንዳሉ የታሪክ መዛግብት ያረጋግጣሉ። ሊመስሉ በማይችሉ መነሻዎች የተጀመሩ ጦርነቶች አድገው በሰው ልጅ ታሪክ ከፍ ያለ ጠባሳ መፍጠር የቻሉ ሰብአዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውድመቶችን አስከትለዋል።

ውስጣዊ ሰላም በሌላቸው፤ ከፍ ባለ የስነ ልቦና ቀውስ በሚሰቃዩ ግለሰቦች እና ቡድኖች የተማጡ፤ ወቅታዊ ማህበረሰባዊ ሁኔታዎች እድል ፈጥረውላቸው የተወለዱ የእብሪት አስተሳሰቦች የፈጠሯቸው የማን አለብኝነትና የንቀት አስተሳሰቦች ዓለምን ያስከፈሉት ዋጋ ዛሬም ቢሆን ከስነልቦናዊ ጠባሳቸው ያገገመ አይደለም።

እነዚህ ግለሰቦች እና ቡድኖች ስለሰላም የሚደረጉ ጥረቶችን የአቅመቢስነትና የተሸናፊነት መገለጫ አድርገው የማየታቸው እብደት ችግሩን የከፋ ከማድረጉም በላይ፤ ውጤቱም ከእነርሱ አልፎ እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ ሳይቀር የመጨረሻ የሚባለውን ዋጋ እንዲከፍል አስገድዶታል።

በአገራችን ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የሚስተዋለውም የዚህ ተጨባጭ እውነታ ማሳያ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ራሱን አይነኬ ጣኦት አድርጎ የሚመለከተውና በዚህ አተያዩ የሳተው አሸባሪው ሕወሓት በህዝባዊ ተቃውሞ ከስልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮ እብሪት በወለደው ደንታ ቢስነትና ማን አለብኝነት አገርን ብዙ ዋጋ አስከፍሏል።

“ጦርነት ባህላዊ ጫወታችን ነው“ ከሚለው የእብደት ተረት ጀምሮ፤ በሴራ ጥርሱን መንቀሉን እንደ አንድ ከፍ ያለ ቡድናዊ እሴት አድርጎ የመውሰዱ እውነታ፤ ስለ ሰላም እና ሰላም ሊፈጥረው ስለሚችለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ደንታ ቢስ እንዲሆን አድርጎታል።

አሸባሪው ሕወሓት በእብሪት በለኮሰው ጦርነት የአገርን ሀብትና ንብረት በእሳት እንዲማገድ አድርጓል፤ ብዙ መስራት፣ ማልማትና ለአገር ነገዎች ተስፋ የሆኑ ዜጎች ሕይወት ለህልፈት እንዲዳረግ አድርጓል። በየቦታው በታመነበት ሴራ በፈጠራቸው ግጭቶች ዜጎች ሰላም እንዲያጡ በማድረግ ማህበራዊ መረጋጋት እንዳይኖር በስፋት ተንቀሳቅሷል።

"አገር ለማፍረስ እስከ ሲኦል እንወርዳለን“ በሚል ለታሪካዊ ጠላቶቻችን የልብ ልብ በሚሰጥ መልኩ በመንቀሳቀስ፣ ለሞት ተስፋቸው ህይወት ለመዝራት ሞክሯል። በዚህም ከተፈጥሯዊ ሞቱ ትንሳኤ የሚያገኝ እስኪመስለው ፍጹም በሆነ ጥፋት ተጉዟል።

ቡድኑ ከሰላም ይልቅ ለጦርነትና ለሴራ ከፍ ያለ ዋጋ መስጠቱ፣ በዚህም በተሰጠው የሰላም እድል ለመጠቀም ፈቃደኝነት ማጣቱ፤ ራሱንና የትግራይ ሕዝብን ጨምሮ አገርንና ህዝብን ያስከፈለው ዋጋ ከፍተኛ ነው። የሕዝቡን የለውጥ መንፈስ ከመረበሽ ባለፈ ለውጡ ተፈጥሯዊ ጉዞውን እንዳይጓዝ የማሰናከያ ድንጋይ ሆኗል።

ሕዝባችን እንደ ሕዝብ ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ ድንገትም ከዛም በፊት በተለያዩ ዘመናትና ትውልዶች ያለመውን ህልሙን እውን ሆኖ በእጁ ለመጨበጥ ከምንም በላይ ሰላም እንደሚያስፈልገው፤ ይህ ሰላም ደግሞ ከጦርነቶች በላይ ዋጋ ሊያስከፍለን እንደሚችልም ይታመናል።

በዘመናት መካከል በምድራችን የተካሄዱ የርስ በርስ ጦርነቶች አንድም ኃይል መፈታተንን፤ ከዛም በላይ የታሪካዊ ጠላቶቻችን እጆች በስፋት የተስተዋሉባቸው ናቸው። ሁለቱም ቢሆኑ የሰላምን ዋጋ በአግባቡ ካለመረዳት የመነጩ፤ የሰላም እጦት ብቻ ሳይሆን ከሰላም የሚገኙ ትሩፋቶችን ጭምር ያሳጡን ናቸው።

ዛሬ ያለንበት ድህነት እና ከዚህ የሚመነጨው ኋላቀርነትና ጠባቂነት የዚሁ ችግራችን አካል ነው። ዛሬ ራሳችንን ለመሆን ለጀመርነው እልፍ አስጨራሽ ትግል ትልቁ ተግዳሮት የሆነብን ይሄው ይዘን የመጣነው ትውልዶችን የምንገብርበት ስለ ሰላም ያለን የተዛባ አተያይ ነው። ስለነገዎቻችንም ተስፈኞች እንዳንሆን እያደረገን ያለው ይሄው ስለ ሰላም የደነደነው ልባችን ነው።

አሁን ግን ከዚህ መንገዳችን ልንመለስ፤ ስለሰላም የደነደነ ልባችንን ስስ ልናደርገው ይገባል። ስለ ሰላም የሚከፈል የትኛውም ዋጋ ስለነገ ተስፋና ስለ ነገ ትውልዶች የሚከፈል ከዋጋዎች ሁሉ ከፍ ያለ ዋጋ እንደሆነ በአግባቡ ማስተዋል ይኖርብናል። ውስጣዊ ሰላም በሌላቸው፤ ከፍ ባለ የስነ ልቦና ቀውስ በሚሰቃዩ ግለሰቦች ተጠልፈን በገዛ ሰላማችን ላይ ጠላት ልንሆን አይገባም። ስለሰላም የሚከፈለውን ሁሉ በመክፈል ነገዎቻችንን ብሩህ እናድርግ!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የኢትዮጵያ አሁናዊ አደጋ

ታምራት ተስፋዬ

ፈረንሳዊው የሒሳብ ሊቅ፣ የፊዚክስ ሊቅ፣ የፈጠራ ባለሙያ፣ ጸሐፊ፣ የሃይማኖት ምሁርና ፈላስፋ ብሌዝ ፓስካል፣‹‹ሰው የተፈጠረው ለማሰብ ነው "ይለናል:: እርግጥ ነው ሰው ማሰብ እንጂ አለማሰብን አይችልም:: አለማሰብ ራሱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ማሰብ ይኖርበታል::

ሰው በህይወት እስካለ ማሰቡን አያቆምም። የሚያስበውን ግን ሊመርጥ ይችላል:: አስተሳሰቡም በተግባርና በምግባሩ ይታያል:: ሲያስብ የተሳሳተ ምግባሩም ሆነ ተግባሩ የተሳሳተ መሆኑም እርግጥ ነው:: ታዋቂው የሥነ ልቦና ባለሙያ ዶክተር ካርል ጁንግ ‹‹Thinking is difficult. That is why most people judge›› ማሰብ አስቸጋሪ ወይም ከባድ ነው:: ብዙ ሰዎች የሚፈርዱት ለዚህ ነው›› ይላል::

እርግጥም ማሰብ የሚከብዳቸው ሰዎች ሰፊውን አለም በጭላንጭል እይታ የሚመለከቱና ቀላሉን የሚመርጡ ናቸው:: የእኔ የሚሉት ሃሳብ የሌላቸው በመሆኑ ከአመክንዮ ጋር ይጋጫሉ:: ምን፣ ለምን፣ እንዴት ? ብለው አይጠይቁም:: እንደጋሪ ፈረስ በማንም ይሾፈራሉ:: ሌሎች ሲፎክሩ ይፎክራሉ:: ጃስ ሲላቸው ይናከሳሉ:: እንያዝ ሲላቸው ያሯሩጣሉ:: በስሜታዊነት ፈረስ በመጋለብ ለጠብ እጃቸውን ለመሰብሰብ እንጂ አንድ ጊዜ እንኳን ለማሰብ ጊዜ የላቸው:: አድርጉ የተባሉ ሁሉ ለማድረግም አያቅማሙም::

በእርግጥ ሁሉም ሰው በራሱ ሃሳብ ትክክል ነው:: ይሑንና አንዳንዶች የእኛ ብቻ ልክ ነው ብለው ስለሚያስብ የሌሎችን ሃሳብ ለመስማትም ሆነ ለማክበር ቦታ የላቸውም:: የሌሎችን ሃሳብም ቢሆን አይመዝኑም:: አይመረምሩም:: ፈትነው አያጣሩም::

በትንሹ ተረድተው በትልቁ ይፈርዳሉ:: ቀድሞ ባወቁት ወይም በተነገራቸው ይደመድማሉ:: ልክነትና ልክነታቸውን ብቻ ያውጃሉ:: ነገር ግን ሃሳብና ምግባራቸው አደባባይ ሲወጣና በሌሎች መመዘን ሲጀምር ትክክለኝነታቸው ጥያቄ ውስጥ ይገባል::

የልክነት ትርጉሙና ፍቺው በአንድም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲታሰብ ደግሞ ማሰብ ብቻም ሳይሆን በምክንያት መሳብም ተያይዞ ይመጣል:: ምክንያታዊነት ደግሞ በተንኮል ያልታጠፈ፣ በምቀኝነት ያልተቆለመመ፣ በራስወዳድነት ያልተንጋደደ ሃሳብና ምግባር ነው::

ምክንያታዊነት፣ አመዛዛኝነት፣ አስተዋይነት ነገሮችን አንድ በአንድ በጥልቀት በማየትና በመመርመር እውን የሚሆን ነው:: ይሕ እንደመሆኑም ምክንያታዊ አስተሳሰብ መያዝ ከባድ ነው:: ይህ በመሆኑም ብዙዎች ምክንያት አልባነትን ይመርጣሉ::

እነዚህ ሰዎችም በምክንያት ለማሰብ ስላልተዘጋጁ ግብረ መልስ ለመስጠት ደመነፍሳቸውን ይጠቀማሉ:: ስሜታቸውን ያስቀድማሉ:: እነሱ ያሰቡት ብቻ ትክክል ይመስላቸዋል:: ጉዳዩን በሌላ ሰው ጭንቅላት ውስጥ ሆነው አይመለከቱትም:: እውነታውን ሳይሆን በእነርሱ የታሰበውን ብቻ የመጨረሻ ልክ አድርጎ ይወስዳሉ::

ምክንያታዊ ባልሆነ አስተሳሰብም ያልተጨበጡና በወጉ ያልተጠኑ ትችቶችን እንደጉድ ያወርዳሉ:: ስለተመለከቱትም ሆነ ስላደመጡት እንዲሁም ስላነበቡት ምንነቱን በቅጡ አይረዱም:: ብቻ በሩቁና በጭፍን ይደመድማሉ:: ታርጋ እየለጠፉ ጎራ ያበጃሉ:: ያለምክንያት ይዘልፋሉ:: ይፈርጃሉ:: ጎራ ፈጥረው ጣት ይቀስራሉ:: እኛና እነሱ የሚል ክፍፍል ይሰራሉ:: እርግማን ያወርዳሉ::

እኔ የኢትዮጵያ አሁናዊ አደጋ "Present danger " ለሁሉም ነገር ምክንያት አልባ ድምዳሜና ግብረ መልስ መስጠት ነው የሚል አቋም ይዣለሁ:: በአሁን ወቅት በኢትዮጵያ ባልጠራ መረጃ ሃሳቡን ሳያጣሩ የሚደመድሙ፣ አንድ ጥግ ቆመው ሌላውን ጥግ የሚያወግዙ በዝቷል::

የሌላውን ሃሳብ ለመረዳት የተዘጉና የተገዘቱት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: ቀድመው የሰሙትን አምነው የተቀበሉና በእሱ ብቻ የሚኖሩ አዲስ ሃሳብ ለመስማት ዝግጁነት የሌላቸው፤ በጠባቡ የሃሳባቸው ዋሻ መሽገውና የሕሊናቸውን በር ዘግተው የተቀመጡ በርካቶች ናቸው::

አሁን ላይ ምክንያታዊነት፣ ሚዛናዊነት፣ አስተዋይነት ገና ያልደረስንበት የሕይወት ጥጋችን ሆናል:: ምክንያታዊ አለመሆን በርካቶች የሚቸኩሉበት ችሎታቸው እየሆነም መጥታል:: ምክንያታዊነት ጠፍቶ ስሜታዊነት ጎልቶ ወጥታል:: በምክንያት አስቦ በምክንያት የሚናገር አንሷል:: ጭፍን ድምዳሜና ችኩል አጠቃሎ ውጦናል:: ድክመትን ብቻ ለመግለፅ፣ የተካነ ትውልድ፤ በአቃቂር ጫፍ የደረሰ ህዝብ በዝቷል::

አሁን አሁን መናገር የህልውናቸው ምስክር ወይም ማረጋገጫ አድርገው የሚወስዱና ካልተናገሩ የሌሉ የሚመስላቸው በርካቶች ናቸው። ስም ጠርቶ ማውገዝ የለም። እስቲ ጥሩት ሲባሉም የሚጠሩት አሁን የለም። እንዴት እንዲህ ይሆናል ሲሉ እንዴት እንዲህ አይሆንም ለሚለው ቦታ የላቸውም:: ሃሳብ፣ ተግባርን ህልማቸው ቡድናዊ፣ በደንብ ሲጠና ደግሞ ግላዊ ነው።

እንደታዘብኩት ከሆነ ምክንያት አልባዎች የሰቀሉትን አውርደን ለመፈጥፈጥ ይቸኩላሉ:: ሲያወርዱም ይጣደፋሉ:: ደካማ ነገር ማጉላት፣ ድክመቱን ማውጣት፣ ክፍተቱን ፈልጎ ማግኘት ይቀናቸዋል:: ይሑንና ጥቅም ጉዳቱን ፈልቅቆ ለማግኘት አቅምም፣ ዝንባሌም ሆነ ፍላጎቱ ያጥራቸዋል:: የኢትዮጵያ አሁናዊ አደጋ "Present danger" ይሕ ነው::

ፉከራቸው ከዕውቀታቸው ጋር ያልተዋሀደ ነው:: ስለሚያወግዙት ግማሽ መንገድ ተራምደው አይጠይቁም:: ማጣጣል እንጂ ማድነቅ ምርጫቸው አይደለም:: ምክንያት አልባነት ሰለባ ተጠቂዎች እንዲህ ብናደርግ ሲባሉ ቢያንስ ሞክረው ውጤቱን ለመመልከት አዋጭ ከሆነ መቀጠል ካልሆነም ለማቋረጥ ዝግጁና ተባባሪነት አይታይባቸውም:: ይልቁንም ሳይጀምሩ ይጨርሳሉ:: የኢትዮጵያ አሁናዊ አደጋ "Present danger" ይሕ ነው::

ይሁንና እኛ ያልነው ብቻ ልክ ነው ሌሎችን አትስሙ በሚል ትችት ብቻ ማዝነብ፣ ከግዙፉ ነጭ ይልቀቅ ነጥቡን ጥቁር በማጉላት የአገርን የብልፅግና ጉዞ ለማደናቀፍ የድንጋይን ሚና መያዝ ተገቢ አይደለም:: እንዲህ ብንደረግስ፣ እንዲህ ሊደረግ ታስቧል እንዲህ ተደረገ በተባሉ ቁጥር ለድምዳሜ መቸኮል የጤነኝነት አይደለም::

መሰል ምክንያት አልባነት አልጫ ነው:: ጣዕም የለውም:: ይሠለቻል:: ኢ- ምክንያታዊ መሆን ነፍስ የለውም:: ምንም አይለውጥም:: አይቀይርም:: አያዘምንም:: አያሰለጥንም:: ለማወቅ ለመመርመር፣ ለመሰልጠን አዳዲስ መንገዶችን ለመፈተሽ ዕድል አይሰጥም:: ጭፍን ድምዳሜ ማንንም አያስተምርም:: አዕምሮ ላይ የሚጨምረው አንዳች ነገር የለውም:: በየትኛውም ጥግ ብንሆን የምንተቸውን ልናውቅ ይገባል::

ምክንያታዊ አለመሆን ሰዎቹ ያሳዩትን መንገድ ብቻ የሙጥኝ ብሎ ከራሱ የሕይወት ጎዳና ጋር ይጠፋፋል:: አንድ ጥግ እንዲቆም የተደረገ አዕምሮ አማራጭ መንገድ የለውም:: በለመደው ጥግ እንደቆመ ጊዜ ያልፍበታል፤ እድሜውም ይባክናል::

አሁን ላይ ኢትዮጵያችን ካሰበችው እንድትደርስ እንደ ጎልያድ መንገድ የሚዘጉና ዘወር ለማድረግ እደ ህዝብ ልናከማቸው የሚገቡና ብዙ ህመሞች አሉብን:: ካሟላነው ይልቅ ያጎደልነው እልፍ ነው:: እንደሐገር ከሰራነው ይልቅ ያልሰራነው ይልቃል::

ይህን ለታሪክ ለመቀየር መተጋገዝ፣ መደናነቅ መተቻቸት ተገቢ ነው:: ይሑንና በዚህ ሂደት ከእያንዳንዱ አስተሳሰብና ተግባራችን ጀርባ ምክንያት መሆንና ምክንያታዊነትን ማስቀደም ግድ ይኖርብናል:: ከሁሉ በላይ የምክንያታዊነት ቁመታችንን ልንሰርዝም ይገባል::

በምክንያት ማሰብ፣ ከድምዳሜ መውጣት የግድ ይለናል:: በምክንያት መውደድና መጥላት፣ መንቀፍና መደገፍ መልመድ ይገባናል:: ጨዋውን ከባለጌ፣ ታማኙን ከከሃዲው፣ አጭበርባሪውን ከሃቀኛው፣ ሙሰኛውን ከደህናው መለየት ይኖርብናል::

ኢትዮጵያችን በአሁን ወቅት ከሚያፈርስ ይልቅ የሚያድስ፣ የመከፋፈል ፋሽን ተቀብሎ የመለያየትን ባንዲራን የማያውለበልብ ትውልድ ትሻለች:: ቀዳዳዋን ከመስፋት ይልቅ የሚያጠብላት ትውልድን ትባጃለች:: የሚያፈርስ ሳይሆን የሚገነባት፣ ጥላቻን፣ መሃይምነትን፣ ቂም በቀልን እንትፍ የሚል በጎ ምግባርንና መልካም ስራን እፍ ብሎ የሚያቀጣጥል ትውልድ ትሻለች:: አሁናዊ አደጋዋን እናስወግድላት:: በጎሰኝነት አስተሳሰብ፣ በመጥበብ ፖለቲካ እናሳዝናት::

ዜና



# ኢትዮጵያን በውክልና ጦርነት ለማዳከም የሚፈልጉ ሃይሎችን ሴራ ሕዝቡ ሊገነዘበው እንደሚገባ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን በውክልና ጦርነት ለማዳከም የሚፈልጉ ሃይሎችን ሴራ ሕዝቡ ሊገነዘበው እንደሚገነባ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ አሳሰቡ።

የ8ኛ ዕዝ በግዳጅ አፈፃፀማቸው ብልጫ ላሳዩ የሠራዊት ክፍሎችና አባላት የሜዳይ እና ዕውቅና መስጠት ሥነ-ሥርዓት አከናውኗል።

በመርሐ ግብሩ ላይ ሽልማት በመስጠት የስራ መመሪያ ንግግር ያደረጉት የጥቁር አንበሳ ጀግና ከፍተኛ ሜዳይ ተሸላሚውና የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ አሸባሪው ሕወሓት ባልዋለበት ገድል ራሱን የሚያጽናና ውግያን ሲያንቀለጳጽስ የሚውል ሃይል መሆኑን ገልጸው በበርካታ አውደ ውግያዎች የደረሰበትን ሽንፈትና ኪሳራ ግን ማንሳት አይፈልግም ብለዋል።

በአሁኑ ሰዓትም በርካታ የውጭ ሃይሎች ሀገራችንን ለማዳከም ሰፊ የውክልና ጦርነት አውዶች መከፈታቸውን አንስተው የነዚህን ሃይሎች ሴራ ሕዝባችን በመገንዘብ ሊያከሽፈው ይገባል ብለዋል።

8ኛ ዕዝ አሸባሪውን የትህነግ ሃይል ለመደምሰስ በታቀደው ዘመቻ ህብረ ብሄራዊ አንድነት ላይ የሠራዊታችን ጠንካራ ክንድ በመሆን በቡድኑ ላይ ከፍተኛ የመመከትና የመደምሰስ ስራውን ሰርቷል።

የዕዙ የሠራዊት አመራርና አባላት በፈጸሙት ገድል አገር ከተደቀነባት የመፍረስ አደጋ መታደግ በመቻላችሁ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል ብለዋል።

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ሃጂ አወል አርባ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሀገር ለማፍረስ የተንቀሳቀሰበትን ሂደት አስታውሰው ይህ ቡድን ለዳግም የክህደት ተግባር ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ደጋግመው ሊያስቡበት ይገባል ብለዋል።

የ8ኛ ዕዝ ዋና አዛዥ ሌ/ጄ አሰፋ ቸኮለ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ዕዙ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም የተዋጊውንና የድጋፍ ሰጪ ክፍሎችን አቅም በመገንባት ለሌሎች እዞች አጋር ክንድ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

ዕዙ በተሰማራበት የግዳጅ ቀጠና አኩሪ የተጋድሎ ታሪኮችን በመስራት ሀገራዊ ሃላፊነቱን መወጣቱን አስታውሰው የዕዙ የሠራዊት አመራርና አባላት ባለፉ ታሪኮች ሳይኩራሩ ቀን ከሌሊት በመስራት አስተማማኝ የዝግጁነት ደረጃን ማረጋገጥ እንደተቻለም ተናግረዋል።

ዕዙ ለ3ኛ ደረጃ ሜዳይ ምርጥ አዛዥ 16፣ ለ3ኛ ደረጃ ምርጥ ተዋጊ 11፣ ለ3ኛ ደረጃ ድጋፍ ሰጪ 26፣ ለምርጥ አሃዱ 4፣ ሁለተኛ ደረጃ ሜዳይ ለምርጥ አዛዥ 31፣ ለምርጥ ተዋጊ 16፣ ለምርጥ ድጋፍ ሰጪ 10፣ ለምርጥ አሃዱ 2 ሜዳልያ ተሸልሟል። የ8ኛ ደቦል ዕዝ በዕለቱ አርማውንና መዝሙሩን በክብር እንግዶች አስመርቋል።

በሥነ-ሥርዓቱ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ ምክትል ጠ/ኢታማዦር ሹም ጀኔራል አበባው ታደሰ፣ የሰሜን ምዕራብ ዕዝ ዋና አዛዥ ጀኔራል ጌታቸው ጉዲና፣ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ሃጂ አወል አርባ፣ ጄነራል መኮንኖችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች መገኘታቸውን ከመከላከያ ሠራዊት ገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ጉባኤው ሕግ የማስከበር ተግባሩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የጉባኤው ጠቅላይ ጸሃፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሳሰቡት፣ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ፊቱን ሰላም ማስፈን እና የሕዝብ ደሕንነት ማስጠበቅ ላይ በማዞር ሕግ የማስከበር ተግባሩን ሊያጠናክር ይገባል።

ሕዝብ ነግዶ እንዲያተርፍና በሰላም ወጥቶ እንዲገባ በአገር ሰላም ሊሰፍን ይገባል ያሉት ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፤ ትዕግስት ጥሩ ቢሆንም ከልክ ሲያልፍ ትእግስት ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን ሕዝቡ በምሬት እያነሳ በመሆኑ ከምንም ነገር በፊት በፊት ሰላም ማስፈን ላይ በትኩረት መስራት አለበት ብለዋል።

እንደ ቀሲስ ታጋይ ገለጻ፤ መንግሥት ሰው በሰላም ወጥቶ እንዲገባና ያለስጋት እንዲንቀሳቀስ ጸጥታን ማስጠበቅ ይገባዋል፣ ከልክ ያለፈ ትእግስቱን መልሶ ጸጥታ ማስጠበቅና ሰላም ማስፈን ይጠበቅበታል። ሕዝቡ የራሴን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚል ወዳልተፈለገ ሁኔታ እንዳይገባ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

መነሻው ምንም ይሁን ምንም ያላግባብ የሰው ሕይወት ማጥፋት በአገሪቱ ሕግም ደረቅ ወንጀል ነው፣ በመንፈሳዊ አስተምህሮትም ሃጢያትም ጥዩፍም ነው። በየትኛውም መልኩ የንጹሃንን ሕይወት የሚያጠፉ ሁሉ እግዚአብሄር ይበቀላቸዋል ብለን እናምናለን ሲሉም ቀሲስ ታጋይ ተናግረዋል።

በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች አንዳንድ ጊዜ የእምነት ሽፋን እየተሰጣቸው ሌላ ጊዜ ደግሞ ማንነትን ሽፋን በማድረግ ንጹሃን ይሞታሉ፤ በተለይ በእጃቸው የጦር መሳሪያ ያልያዙ፣ የፖለቲካ ልሂቃንና የፖለቲካ ስጋት ያልሆኑ አካላት የፖለቲካ አጀንዳ ባነገቡና ጽንፍ በያዙ የታጠቁና የተደራጁ ቡድኖች ሕይወታቸውን ያጣሉ፤ ይህ ደግሞ ፍጹም መሆን የሌለበት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአማኞች አገር መሆኗ ይታወቃል፣ የሃይማኖት ስራ እየሰራንም ፈጣሪ ያዘዘውን ካልፈጸምን ደግሞ ድርብ ወንጀል ይሆናል። በስጋችንም በመንፈሳችንም እንቀጣበታለን ያሉት ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ድርጊቱ የተወገዘ በመሆኑ ሊቆም እንደሚገባው አሳስበዋል።

በማንነት ሽፋን፣ በብሽሽቅ ፖለቲካ አራማጆች መንገድም ንጹሃንን እያጠፉ መንግሥት ለመሆን የሚደረገው ሩጫም ፈጽሞ የሚሳካ እንዳልሆነ ሊቀትጉሃን ቀሲስ ታጋይ አሳስበዋል።

ችግሮች ካሉ በውይይት፣ በሰላማዊ መንገድ መፍታት ያስፈልጋል። ዜጎችን አጋጭተውና አጋድለው የመንግሥትንና የዜጎችን ሀብትና ንብረት በማውደምና በማቃጠል ወደ ሥልጣን ለመውጣት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተቀባይነት የላቸውም ሲሉም ተናግረዋል።

ነገ ወደ ሥልጣን ቢመጡም የሚመሩትን ሕዝብ ከጨረሱ በኋላ እንመራለን ማለት የማይሳካ በመሆኑ ራስን መመርመር ተገቢ ነው ያሉት ሊቀትጉሃን ቀሲስ ታጋይ፤ እንዲህ አይነት ፍላጎቶችን ለማሳካት በተለያዩ ሚዲያዎች የሚደረጉ ቅስቀሳዎችም መቆም ይገባቸዋል ብለዋል። በሰላም፣ በአብሮነትና በመከባበር የጋራ እሴቶቻችን ዙሪያ መቆየትና አብረን መስራት ይጠበቅብናል ሲሉም አሳስበዋል።

ጉባኤው በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍልም ጦርነቱ ከመካሄዱ አስቀድሞ ወደ ግጭት እንዳይገባ፣ የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ፣ ንብረት እንዳይወድምና ችግሩ በሰላማዊ ውይይት እንዲፈታ ጥረት ማድረጉን አስታውሰው፤ ሆኖም አባቶችንና የሃይማኖት ተቋማትን ባለመስማት ፍጻሜው ጥፋት መሆኑ እየታየ ነው ብለዋል።

በወለጋ ዙሪያ ለኦሮሞ ነጻነት እንታገላለን የሚሉ አካላትም ሆኑ ሌሎች በነጻነት ስም ታጥቀው በንፁሃን ላይ ጭፍጨፋ የሚፈጽሙ አካላት፣ አሉ የሚሏቸውን ችግሮች ለመፍታት በነፍጥና በሃይል ሳይሆን ሰላማዊ ትግልን ሊከተሉ እንደሚገባ እና ዜጎች ላይ ችግር እንዳይደርስ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸውም መከረዋል።

# “ሕወሓት መንግሥት የሰጠውን የሰላም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አሸባሪው ሕወሓት ከተፈጥሮ ባህሪው አኳያ ሲታይ ችግሮችን በውይይት የመፍታት ልምድ የለውም ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ያለ ጦርነት መኖር የማይችል ሃይል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ ችግሮችን ሁሉ በጉልበት እፈታለሁ ብሎ የሚያምንና ይህንንም ሲተገብር የመጣ ድርጅት ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ መነሻነት ውይይቱ ተሳክቶ የትግራይ ሕዝብ ችግርና ስቃይ ይፈታ ይሆን ? የሚለው ጉዳይ ያሰጋኛል ብለዋል፡፡

መንግሥት አሁንም እያደረገ ያለውና ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ሲያደርገው የነበረው የሰላም አማራጭ ጥሪ ሆደ ሰፊነቱን የሚያሳይ መሆኑን አውስተው፤ አሁንም የሰሜን ችግር በውይይት ካልተፈታ የትግራይ ሕዝብ ችግሮች ይባባሳሉ፣ እየከፉ ይሄዳሉ ብለዋል፡፡

ቡድኑ የትግራይ ሕዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል፣ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ጥቅም ያለው በማስመሰል ለራሱ ጥቅም ሲል መያዣ አድርጎ እየተጠቀመበት መሆኑን ጠቅሰው፤ የእኛ ፓርቲ የትግራይ ሕዝብ ጥቅም በሕወሓት የሴራ አካሄድ ሊረጋገጥ ስለማይችል ይህንን ቡድን ማስቆም እንደሚገባ ያምናል ብለዋል፡፡

በትግራይ ሕዝብ ላይ ለተከሰቱት ችግሮች ሁሉ መነሻ ምክንያቱ የሕወሓት ቡድን ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ካለው ቀደኛ ጠላቱ ሕወሓት ነው ያሉት ሃላፊው፤ ይህን ሃይል ከትግራይና ከኢትዮጵያ ፖለቲካ መወገድ አለበት ብለን እናምናለን ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ አሁን ለገባበት ችግር ተጠያቂው ሕወሓት መሆኑን አመልክተው፤ ሕዝቡ ከገባበት ችግር ለመውጣት ቡድኑ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ሊያስገድደው አልያም ዞር በል በማለት ተደራጅቶ ሊታገለው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ጠላት የለውም፡፡ የሕወሓት ቡድን የፈጠራቸው ትርክቶች ሁሉ ውሸትና የእሱን ጥቅም ብቻ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው፡፡ ሕዝቡ ከሕወሓት የውሸት ፕሮፖጋንዳ ራሱን ነጻ አድርጎ ጠላቱ እሱ ብቻ መሆኑን አውቆ መታገል አለበት ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የትግራይ ሕዝብ ለሕወሓት የሽብር ቡድን ጥቅምና ሥልጣን ሲባል ብቻ ከዚህ የበለጠ ዋጋ መክፈል የለበትም ብለዋል፡፡

በመንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተፈጠረው ልዩነት በሰላም እንዲፈታ የለውጡ መንግሥት ብዙ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ አሸባሪው ሐወሓት የሰላም ጥሪን አልቀበልም ብሎ ወደ ጦርነት መግባቱንም አስታውሰዋል፡፡

# ‹‹ታሪካችንን የማይመጥኑ እኩይ ድርጊቶችን እያወገዝን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ነው፡፡ ታሪካችንን የማይመጥኑ እኩይ ድርጊቶችን እያወገዝን በዓለም ተወዳዳሪና የምንኮራባት ኢትዮጵያን መገንባት የእኛ ኃላፊነት ነው፡፡

ተመራቂ ተማሪዎች በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል እውቀት በዩኒቨርሲቲው ቆይታችሁ ቀስማችኋል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ዛሬ ከዩኒቨርሲቲ ሕይወት ወደ ኃላፊነት ሕይወት የምትሸጋገሩበት ምዕራፍ ነው፤ “የእናንተ የህሊና እርካታ የሚለካው ወደ ስራው ዓለም በተሰማራችሁበት የሙያ መስክ በምትወጡበት ሙያዊ ኃላፊነት ነው” ብለዋል።

ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማራመድ የሁሉንም ወገን በኃላፊነት መስራትን ይጠይቃል ያሉት አቶ ደመቀ፤ በዚህ ወቅት አገርን የሚያኮሩና የሚያበረታቱ ውጤቶች እየተሰሩ ሲሆን በሌላ በኩል ኢትዮጵያን የማይመጥኑ አንገት የሚያስደፉ የዜጎች ጉዳትን እያስተናገድን እንገኛለን። እርስ በእርስ መጎዳዳትና መጨካከን ታሪካችን የማመጥን፣ የአባቶቻችን እሴት የማይገልጽ አሳፋሪ ድርጊት በመሆኑ ሁሉም ሊያወግዘውና ሊታገለው ይገባል ብለዋል፡፡

ታሪካችንን የማይመጥኑ እኩይ ድርጊቶችን እያወገዝን በዓለም ተወዳዳሪና የምንኮራባት ኢትዮጵያን መገንባት የእኛ ኃላፊነት ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ በዚህ ታሪካዊ ጊዜ ይህ ትውልድ ብዙ ኃላፊነቶችና አደራዎችን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ አገር ተወዳዳሪና ጠንካራ የሚሆነው ተለዋለዋጭና ተገማች ባልሆነው ዓለም ውስጥ በቴክኖሎጂ መወዳደር በገበያው ውስጥ ብቁ ሆኖ መገኘት ሲቻል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያን የምናስከብረው በአንድነታችንና በጽናታችን መሆኑን የገለጹት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጠናውና በዓለም ጠንካራ አገር እንገባ ከተባለ እያንዳንዱ ሳይንስቲስት፣ ተመራማሪ፣ ማሕበረሰቡና ሌላው ዜጋ ጭምር በአገር ጉዳይ ላይ መተባበር ይገባዋል፡፡ ‹‹ተመራቂዎች ወደ ስራው ዓለም ስትሰማሩ ለዚህ አይነት ኃላፊነት መጽናት ይኖርባችኋል›› ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ደረጀ እንግዳ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ ዩኒቨርሲቲው “ዩኒቨርሲቲ ለኢንዱስትሪ” የሚል መርህ አንግቦ እየሰራ ነው። የዛሬ ተመራቂዎች የነገ አገር ገንቢ በመሆናችሁ በዩኒቨርሲቲው ያገኛችሁትን እውቀት በታማኝነት በተግባር ማሳየት ይጠበቅባችኋል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በአራት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር 8 የልህቀት ማዕከላትን እየገነባ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ተመራቂ ተማሪዎች በስራ ዓለም ሆነውም ዩኒቨርሲቲውን እንዲደግፉ ጥሪ አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ለ8ኛ ዙር በመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ በመደበኛው፣ በተከታታይ በማታና በእረፍት ቀናት ያስተማራቸውን አንድ ሺ 474 ተማሪዎችን አስመርቋል።

በዩኒቨርቲው በየትምህርት ክፍሎቹ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ከአቶ ደመቀ መኮንን፣ ከዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ማሞ ምህረቱ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ የዋንጫና የሜዳሊያ ሽልማት ተቀብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በዚህ ወቅት በአምስት ኮሌጆችና በ13 የትምህርት ክፍሎች በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ስምንት ሺ 128 ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር ላይ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በአዲሱ የከፍተኛ ትምህርት ልየታ መሰረት የምርምር ዩኒቨርሲቲ መደብ ውስጥ የተካተተ ሲሆን በዘርፉ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ዩኒቨርሲቲው በአጠቃላይ ባለፉት 10 ዓመታት 11 ሺ 50 ተማሪዎችን እንዳስመረቀ ታውቋል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## የቋጠሯችን ሁሉ መፍቻ

አራተኛው ዙር አገር አቀፍ የአረንጓዴ አሻራ ማስጀመሪያ መርሐግብር በጉለሌ እጽዋት ማዕከል እጅግ በሚገርምና እጅን በአፍ በሚያስጭን ልምላሜንና ተስፋን በሚያጋባ መድረክ ተከናውኗል። ባለፉት ሶስት አመታት ከ18 ቢሊየን በላይ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን ዘንድሮ ደግሞ ከስድስት ቢሊየን በላይ ይተከላሉ ተብሎ ይጠበቃል። ለተከላ ከተዘጋጁት 52 በመቶ የሚሆኑት ችግኞች የምግብ ዋስትና የሚያረጋግጡ መሆናቸው ይች አገር በሚቀጥሉት ሶስትና አራት አመታት ከፈጣሪ ጋር ልምላሜዋና በረከቷ የሚያስገርምና ተዝቆ የማያልቅ እንደሚሆን ከወዲሁ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል። በአራት አመታት 20 ቢሊየን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ የነበር ቢሆንም ዘንድሮ ዕቅዱን ከማሳካት ታልፎ ከሁለት ቢሊዮን በላይ ተጨማሪ ችግኞች ይተከላሉ።

በጉለሌ የዕጽዋት ማዕከል የተዘጋጀውን የ4ኛ ዙር" ኢትዮጵያን እናልብሳት ! " የአረንጓዴ አሻራ ማስጀመሪያ ስነ ስርዓት መድረክ እጅን በአፍ በሚያስጭን ልምላሜና በአበባ አጊጦና ምድራዊ ገነት መስሎ ትንግርተ ውበት ተጎናጽፎ ስመለከት፤ ሁለት ነገሮች በአእምሮዬ እየተመላለሱ ነበር። የመጀመሪያው ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ከአራት አመታት በፊት ያስጀመሩት "አረንጓዴ አሻራ" ከአመታት በኋላ አገራችንን ቀይሮ ምን ሊያስመስላት እንደሚችል ፍኖተ ካርታውን አበክረው በዛ ለማመን በሚቸግር መድረክ ማመላከታቸው። ሁለተኛው ከዚህ ከአይነ ህሊና የማይጠፋ ሁነት ጀርባ ሁል ጊዜ የሚገርመኝና የሚደንቀኝ አንዳንድ ጊዜም ግራ የሚያጋባኝ የጠቅላይ ሚንስትሩ የመሪነት ተክለ ሰብዕና ነው።

ሰማይ ዝቅ ቢል ምድር ከፍ ቢል አይናቸውን ከትልቁ ስዕል ያለማንሳት ልዩ ሰብዕናቸው። በዚህ ሁሉ ደባ፣ ሴራ፣ ቀውስ፣ መርዶ፣ ዋይታ፣ ለቅሶ፣ ሟርት፣ ጫና፣ ከበባ፣ ጥላቻ፣ ልዩነት፣ በሬ ወለደ፣ ወዘተረፈ አይንን ከትልቁ ስዕል ያለማንሳት፤ በሁኔታዎች ከአገራዊ ህልም ያለመባተት ሰብዕና መላበስ ምንኛ መታደል ነው የሚል መንፈሳዊ ቅናት ይፈጥራል። ውሽንፍሩ ቢበዛ፣ ሰማዩ ቢያጉረመርም ትኩረትን ከራእይ ያለመንቀል የአመራር ተሰጥኦ። ማዕበሉና ወጀቡ ጀልባዋን ቢያናውጠው በዚህ ሁሉ መሀል ካለሙት ለመድረስ በጽናት የመቅዘፍ ሰብዕና። አጀንዳን ለማስጣል ከተደረገና ከሚደረግ ህልቆ መሳፍርት የሌለው ጥረትና ርብርብ ጋር ግብግብ እየገጠመና እየተናነቀ አይንን ከተራራዋ ጫፍ ያለመንቀል የመሪነት ሰብዕና በእውነት ምንኛ መታደል ነው። ውሽንፍሩ ቢበዛ፣ ሰማዩ ቢያጉረመርም ትኩረትን ከራእይ ያለመንቀል የአመራር ተሰጥኦ። ማዕበሉና ወጀቡ ጀልባዋን ቢያናውጠው በዚህ ሁሉ መሀል ካለሙት ለመድረስ በጽናት የመቅዘፍ ሰብዕና። አጀንዳን ለማስጣል ከተደረገና ከሚደረግ ህልቆ መሳፍርት የሌለው ጥረትና ርብርብ ጋር ግብግብ እየገጠመና እየተናነቀ አይንን ከተራራዋ ጫፍ ያለመንቀል የመሪነት ሰብዕና።

ሸኔና ጭፍራዎቹ በምዕራብ ወለጋ፣ በጋምቤላና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ያን ለመስማት የሚሰቀጥጥ፤ ለማየት የሚዘገንን ጭፍጨፋ በፈጸሙበት ማግስት፤ ትህነግ በሰሜን ዕዝና በአገር ላይ ክህደት በፈጸመበት፣ በሉዓላዊነትና ሕግን በማስከበር ዘመቻ ወቅት፤ በግብጽ ፉከራ፣ በሱዳን ወረራ፣ በምዕራባውያን ከበባ፣ በሱዳን ትንኮሳና ወረራ፣ በአለማቀፍ ሚዲያውና በመብት ተቆርቋሪዎች ያ ሁሉ ማጠልሸት በተባባሰበት እንኳ ለአፍታ አይንን ከትልቁ ስዕል ያለማንሳት ተክለ ሰብዕና። ከሳምንት እስከ ሳምንት፣ ከወር እስከ ወር እንዲሁም ከአመት እስከ አመት መሪ፣ አገርና ሕዝብ በሀዘን ልቡ ደምቶ፣ ቅስሙ ተሰብሮ እና ቆዝሞ ከሀዘን ድንኳን አዙሪት እንዳይወጣ የተሸረበን ሴራ በጣጥሶ አይኑን ከከፍታው ጫፍ ያላነሳ።

አረንጓዴ አሻራ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ፣ ሸገርንና እንጦጦን የማስዋብና የማልማት፣ የጣና የወንጪና የኮይሻ አገር አቀፍ ፕሮጀክቶች ትልም፣ የብር ለውጥ፣ ወደ አገራች የቴሌኮም ኢንዱስትሪ አዲስ ተዋናይ ማስገባት፤ የአዲስ አበባ ሜጋ ፕሮጀክቶች፣ የታላላቅ ፕሮጀክቶች ጅማሮ፣ ሒደትና ማጠናቀቅ፣ ወዘተረፈ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ፣ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ፣ ሕጎችንና አዋጆችን ማሻሻል አዳዲስ አዋጆችን ማውጣት፣ አገራቀፍ ምርጫ ማካሄድ እና የመሳሰሉት በርካታ ተግባራትን ለተመለከተ አገሪቱ ውስጥ አይደለም የማያበራ ቀውስ ኮሽታ ያለ አይመስልም። በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስለ ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ሰላምና በመደመር ወደ ብልጽግና ስለመሻገር ሳያሳስቡ ቀርተው አያውቁም። ይህን ፈተና እንደምንሻገረው በልበ ሙሉነት ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው።

ቀውስ ጠማቂዎችና ስፖንሰር አድራጊዎቻቸው የጠቅላይ ሚንስትር አይን ከትልቁ ስዕል አለማንሳት የእግር እሳት ሆኖ የሚለበልባቸው ይመስለኛል። ጥቃቱን አባብሰው የሚቀጥሉትም በዚህ እልህና ቁጭት ሳይሆን ይቀራል። የአዘቦቱ ዜጋ ሆነ ልሒቃኑ ይህን በቅጡ የተገነዘቡት አይመስለኝም። ለዚህ ነው ጠቅላይ ሚንስትሩ ሁሉንም እርገፍ አድርገው ትተው ለምን ከአመት እስከ አመት ፍራሻቸውን አንጥፈው ሀዘን አልተቀመጡም፤ አላስተዛዘኑም፣ አላጽናኑንም የሚል የተሸናፊነትና የተንበርካኪነት ውርክብ ውስጥ የገቡት። ይህ ውልውል በተወሰነ ደረጃ ተገቢነት አለው። ጠቅላይ ሚንስትር በዕለቱ ባገኙት አጋጣሚ ሀዘናቸውን ገልጸዋል። አውግዘዋል። ሆኖም የሐዘን ቀን ያላወጁት፤ ሰንደቃላማ ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ያላደረጉት የንጹሐን ህይወት አልገዳቸው ብሎ ሳይሆን በጠላቶቻችን ፊት ተሸናፊ መስሎ ላለመታየት እና እውቅና ላለመስጠት ይመስለኛል።

የንጹሐን ህይወት መቀጠፍና መፈናቀል አልያም ንብረት መውደምና መዘረፍ ግድ አልሰጣቸው ብሎ ወይም ሀዘኑ ሀዘናቸው አልሆን ብሎ አይደለም። ለጥፋት ኃይሎች ምንም ብታደርጉ ለውጡ ዳር ይደርሳል። የኢትዮጵያ ብልጽግና ለአፍታ እንኳ አይቆምም። ምንም ምድራዊ ኃይል አያስቆመንም የሚል መልዕክትን ለማስተላለፍ፤ እንደ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ለጠላቶቻችን አንበገርም በማለት ሕዝብ ሞራሉ እንዳይጎዳና የተሸናፊነት ስሜት እንዳይጋባባት ጠቅላይ ሚንስትሩ ጥርሳቸውን ነክሰው ሀዘናቸውን ውጠው አይናቸውን ከፍተው ላይ ማድረግን መርጠዋል ብዬ አምናለሁ።

እንደ አባት የልጅን፣ እንደ ባል የሚስትን፣ እንደ ልጅ የእናት የአባት፣ እንደ ወንድም የወንድምና የእህት፣ እንደ ኢትዮጵያዊ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሞት፣ ጉዳት፣ መነቀል፣ መፈናቀል፣ ወዘተረፈ አልሰማቸው ብሎ አይደለም። በጠላቶቻችን ፊት ተሸናፊ መስሎ ላለመታየት እንጂ። የሆነ ቦታ ጥቃትና ጭፍጨፋ የተፈጸመ ሰሞን ቅስማቸው እንደሚሰበር፤ ፊታቸው እንዴት እንደሚጠቁር በቴሌቪዥን መስኮት እየተመለከትን ነው። ለነገሩ የሐዘን ቀን ይታወጅ፣ ሰንደቃላማ ዝቅ ብሎ ይውለብለብ ቢባል እንደ አገርም ሆነ ሕዝብ አራቱን አመታት ሙሉ ሁሉን እርግፍ አድርገን ትተን ሀዘንተኛ ልንሆን ነበረ ማለት ነው። ይህን በማድረግ የጠላቶቻችንን አጀንዳ አስፈጻምን ማለት ነው።

ከ10 አመታት በፊት አልቃይዳ በአሜሪካ ላይ የመንገደኞችን አውሮፕላን ጠልፎ በኒውዮርክ ከአለም የንግድ ድርጅት መንትያ ሕንጻዎች ጋር በማላተም፤ በፔንታጎንም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች ያ ዘግናኝ ጥቃት ሲፈጽም የወቅቱ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ዋሽንግተን በሚገኝ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአንዱ ክፍል ተገኝተው ለተማሪዎች መጽሐፍ እያነበቡ እያለ ከደህንነት ሰዎቻቸው አንዱ የሽብር ጥቃት እየተፈጸመ እንደሆነ ሹክ ይላቸዋል። ፕሬዚዳንቱ ምንም እንዳልተፈጠረ ለልጆቹ የጀመሩላቸውን ንባብ ጨርሰው ተሰናብተው ይወጣሉ። መሪ እንዲህ ስሜቱን ተቆጣጥሮና ዋጥ አድርጎ አገሩን ወደ ዘላቂ መፍትሔ የሚወስድ፤ ደንብሮ ሕዝቡን የማያስደነብር፣ ተሸብሮ ሕዝብን የማያሸብር፣ ተንበርክኮ ሕዝቡን የማያንበረክክ መሆን አለበት የሚባለው ለዚህ ነው። ሌላ አብነት ላክል።

ማዲባ (ኔልሰን ማንዴላ) በረራ ላይ እያሉ ያልተጠበቀ አስደንጋጭ ነገር ይፈጠራል። ይጓዙበት የነበረ አውሮፕላን አንደኛው ሞተር ይጠፋል። አብራሪዎች፣ አብረዋቸው የነበሩ ባለስልጣናትና አጃቢዎቻቸው ይይዙት ይጨብጡት ይጠፋባቸዋል። ማዲባ ግን ምንም እንዳልተፈጠረ የጀመሩትን መጽሐፍ ተረጋግተው ያነባሉ። በዚህ ሁሉ ጭንቅና ጥብ የማዲባ ፍጹም መረጋጋትና አለመረበሽ ከማስገረም አልፎ ግራ አጋብቷቸዋል። አብራሪዎች የካበተ ልምድ ያላቸው ነበሩና ከብዙ ጥረትና ድካም በኋላ አውሮፕላኑን እንደምንም በአንድ ሞተር በሰላም ማሳረፍ ይችላሉ። በዚህም አብራሪዎች፣ ተሳፋሪዎች፣ የበረራ አስተናጋጆች ደስታዎችን በጭብጨባ፣ በሆታና በፉጨት ይገልጻሉ። አሁን ግን ማዲባ የደስታቸው ተካፋይ ሆኑ። ይህን የታዘቡ ጓዶቻቸው ታዲያ እንደዛ ስንጨነቅ ምን እንዳልተፈጠረ የሆንኸው ለምንድን ነው ሲሉ ይጠይቋቸዋል። ከሁላችሁም በላይ የደነገጥሁና የፈራሁት እኔ ነበርሁ። ነገር ግን እናንተን ይበልጥ ማስጨነቅ ስላልፈልጉህ ፍርሀቴን ዋጥ አድርጌ ምንም እንዳልተፈጠረ አስመሰልሁ።

የአሜሪካ ታዋቂ የፕሬዚዳንቶች ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ/presidential Historian/ዶሪስ ኬርነስን "Leadership in Turbulent Times the Lessons of Presidents"በተሰኘ ግሩም ድንቅ መጽሐፏ በዚህ አጋጣሚ ያላነበባችሁት አፈላልጋችሁ እንድታነቡት እጋብዛለሁ ፤ አብርሀም ሊንከን ፣ ቴዎዶር ሩዝቬልት ፣ ፍራንክሊን ሩዝቬልትና ሊንደን ጆንሰን በግል ህይወታቸውም ሆነ በፕሬዚዳንትነታቸው የገጠሟቸውን ኅልቆ መሳፍርት የሌላቸውን ፈተናዎች እንዴት በጽናትና በጥበብ አልፈው ለውጤት እንደበቁ ታስረዳለች። ለዚህ ነው ዶሪስ ከአንድ መሪ ስለሚጠበቁ ባህሪያት ስታወሳ ሁል ጊዜ "ለፈተናዎች አለመበገር" የሚለውን ቀድማ የምታወሳ። "ኢትዮጵያን እናልብሳት!"ብዬ ጀምሬ ስጠፋ " ኸረ ወደ ገደለው !?"አትሉኝም፤

አገራችን በታሪኳ ከፈጸመቻቸው እየፈጸመቻቸው ካሉ ግዙፋን ፕሮጀክቶች ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጨምሮ አንድ ላይ ቢደመሩ የ" አረንጓዴ አሻራ "ን ያህል ክብደት አልሰጣቸውም፡፡ የህዳሴውም ሆነ የሌሎች ታላላቅ ግድቦች ህልውና እንዲሁ 80 በመቶ አገሬው ኑሮ የተመሰረተበት ግብርና እጣ ፈንታ የሚወሰነው ዛሬ በትጋት በምንከውነው የአካባቢ ወይም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ነውና፡፡ በቀደሙት ሶስት አመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ አገር በቀል ችግኞችን ለዛውም ከሞላ ጎደል ስነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረጉ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች መትከል ተችሏል፡፡ ከተተከሉ ችግኞች መካከል እንደ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ ፓፓየ፣ ሙዝ እንዲሁም ቡና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በአራቱም ዙር ከ90 ሚሊየን በላይ ሕዝብ በችግኝ ተከላው ተሳትፏል።

ችግኝ ተከላ የአየር ንብረት ለውጥን፣ የአለም ሙቀት መጨመርንና የአካባቢ ጥበቃ ችግሮቻችንም ሆነ ድህነትን፣ የምግብ ዋስትና ጉድለትን፣ የምርታማነት ተግዳሮትን፣ ድርቅን፣ ርሀብን፣ የዝናብ መቆራረጥንና መቅረት፣ የውሀ እጥረትን፣ የኑሮ ውድነትን፣ በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና በምርት አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተትት፣ ስራ አጥነት፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን፣ የጸጥታና የደህንነት ችግርን፣ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር በማሳለጥ እና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማለም መስፈንጠሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡ ለዚህ ነው ችግኝ ተከላን የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻ ማስተር ኪይ ነው የምለው፡፡

በየአመቱ በአገራችን ከ92ሺህ ሔክታር መሬት በላይ ደን ይመነጠራል። ይጨፈጨፋል። በዚህ የተነሳ የደን ሽፋናችን ከ50 አመታት በፊት ከ35 በመቶ ከነበረበት ደረጃ ወደ ሶስት በመቶ አሽቆልቁሎ ነበር። ለዝናብ እጥረት፣ ለድርቅና ለከባቢ አየር ለውጥ ተዳረግን። በየአመቱ ምርታችን ከ10 በመቶ በላይ መቀነስ ጀመረ። በየአመቱ ከ35 እስከ 40 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይቀንሳል። ሆኖም ባለፉት ሶስት አመታትም ሆነ ከዚያ በፊት በተከናወኑ የችግኝ ተከላና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች የደን ሽፋኑን ወደ 17 በመቶ ማገገሙ ይበል የሚያሰኝ ነው።

### እንደ መውጫ

የበጋ ስንዴ፣ የኩታ ገጠም ግብርናን፣ በተወሰነ ደረጃ ስነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረገ የቴክኖሎጂና የሜካናይዜሽን እገዛ፣ የከርሰና የገጸ ውሃን አሟጦ የመጠቀም፣ ፍራፍሬና አትክልት ላይ ለመስራት፣ በተለይ ከአለፈው አመት ጀምሮ የከተማ ግብርና ትኩረት ማግኘቱ፤ በአርብቶ አደሩ የሚገኙ ጦም ያደሩ ሰፋፊ መሬቶችን በመስኖ ለማልማት አበረታች ጥረትና ርብርብ መደረጉ እና ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ለማስቀረት ግብ መጣሉ የአተያይ ለውጥ በማምጣቱ ተስፋ ያስቆረጠን ግን ደግሞ ብቸኛ ሊባል በሚችለው ግብርና ከምግብ ዋስትና ባሻገር ተስፋችንን እንድናድስ አድርጎናል፡፡ ለዚህ ነው ተስፋ ሰጭ ጅምር እውቅና መስጠት የሚያስፈልገው፡፡

ችግሮቻችንን ሁሉ ፈታተን፣ በታትነንና አገላብጠን ብንመረምራቸው አብዛኞዎቹ ከአንድ ቅርጫት የሚገኙ ናቸው፡፡ የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ ካለመንከባከብ፣ ካለመጠበቅና ካለማልማት ቅርጫት፡፡ የአለም ሙቀት መጨመርን ተከትሎ በመጣ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የተፈጥሮ ሀብታችን እየተጎሳቆለ በመምጣቱ ማለትም መሬታችን የተራቆተ፣ ዝናባችን የአጠረና የተቆራረጠ በመሆኑ የከርሰና የገጸ ምድር ውሃችን በመመናመኑ ግብርናው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም፡፡

በዚህ የተነሳ በግብርና ላይ የተመሰረተው የዜጋው ህይወት፤ የአገሪቱ ልማት ችግር ላይ ወድቋል፡፡ ይህ የሀብት ውስንነትን ፈጥሯል፡፡ በዚህ የተነሳ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከአመት አመት እየተባባሱ መጡ፡፡ እነዚህን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የተፈጥሮ ሀብታችን እንዲያገግም ሌት ተቀን መሰራት አለበት፡፡ መሬት ማገገም፣ ውሃ መያዝ አለባት፡፡ ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው ችግኝ በመትከልና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በስፋት በማከናወን ነው፡፡

" አረንጓዴ አሻራ " የበሽታውን ምልክት ከማከም ይልቅ መነሻውን በማያዳግም ሁኔታ የመፈወስ አቅም እንዳለው በማመን ነው፤" አረንጓዴ አሻራ ! " የእንቆቅልሾቻችን ሁሉ መፍቻ ቁልፍ (ማስተር ኪይ) የምለው፡፡

ከኢትዮጵያ አምላክ ጋር መጭው ዘመን ጥሩ ይሆናል !!!

አሜን።

# የሕይወት ገጽታ

# ወታደሯና ጋዜጠኛዋ ጸሃይ ተፈረደኝ

**እፀገነት አክሊሉ**

እንደ ሪፖርተር መረጃ ሰርሳሪ፤ ማራኪ ፕሮግራመኞችን ቀማሪ፤ እንደ አርታኢ (ኤዲተር ) መንገድ መሪ፤ እንደ ጉዞ ዘጋቢ አገር ዟሪ፤ እንደ ሴት የጽናት አስተማሪ ፤ በቤቷ ደግሞ ጥሩ ሚስትና እናት ናት ይሏታል የሙያ አጋሮቿ አንጋፋዋን ጋዜጠኛ ጸሃይ ተፈረደኝ::

ጋዜጠኛ ጸሀይ ተፈረደኝ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ኢትዮጵያን እንቃኛት በሚል ፕሮግራም ላይ ረጅም ዓመትን ሰርታለች፤ በሴቶች ዙሪያ በሚሰራው የሴቶች መድረክ ፕሮግራሚም በብዙዎች ትታወሳለች:: ላንቺና ላንተ በሚል ፕሮግራሚም ብዙዎች እናውቃታለን :: ለአብነት እነዚህን አነሳን እንጂ ጸሃይ የሰራቻቸው ፕሮግራሞች በርካታ ናቸው::

እኛም ይህ የሙያ ትጋቷ የህይወት መንገዷ ለብዙዎቻችን አርአያ ይሆናል በማለት የዛሬ የህይወት ገጽታ አምዳችን እንግዳ አድርገናታል::

ጋዜጠኛ ጸሀይ ተፈረደኝ የተወለደችው ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ በምትገኘው ሆለታ ከተማ ነው:: ነገር ግን ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ መርካቶ ላይ ነው:: እንደ አለመታደል ሆኖ ጸሃይ እናትና አባቷን ገና በጠዋቱ ነው ያጣቻቸው፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ ከእናትና አባት የሚወለድ እህትም ሆነ ወንድም የላትም:: ነገር ግን ደጓ አክስቷ ወስደው አሳደጓት፤ እሳቸውም ያለቻቸው አንዲት ሴት ልጅ ናትና ጸሀይም አንድ እህት አለችኝ ትላለች::

የሶስት ወይንም የአራት ወር ህጻን ሆና ከመጣችባት አዲስ አበባ ከተማም እየኖረች እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ በቀጥታ ያመራችው ተክለሃይማኖት አካባቢ ወደ ሚገኘው ንጉስ ወልደጊዮርጊስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው:: ትምህርቷን እዚህ ትጀምር እንጂ ከሶስተኛ ክፍል አልዘለለችም:: ቤተሰቦቿ ሌላ ትምህርት ቤት መቀየር አለባት በማለት ልደታ አካባቢ በሚገኘው ተስፋ ኮከብ ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ትምህርቷን እንድትቀጥል አደረጓት::

".... ንጉስ ወልደጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ለቤቴ በጣም ቅርብ ነበር፤ ነገር ግን ቤተሰቦቼ ትምህርት ቤት እንድቀይር አድርገውኝ ልደታ አካባቢ ወዳለው ተስፋ ኮከብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሄድኩ፤ ከቤቴ ከተክለሀይማኖት ተነስቼ ልደታ እስከምደርስ ድረስ አካባቢው ጫካ ነው ሰውም ብዙም የለም፡፡ መንገዱም ቀጫጭን ነው፤ ይህ ደግሞ ለእኔና ለጓደኞቼ ምቹ ነበር፤ ሁላችንም ከቤታችን ገመድ ይዘን በመውጣት በዛ ሜዳ ላይ እየዘለልን እየቦረቅን መንገድ ላይ ቆም እያልን እየተጫወትን በጣም በደስታ ነበር ትምህርት ቤት ደርሰን የምንመለሰው፤ ውይ ሳስበው ራሱ በጣም ነው ደስ የሚለኝ" ትላለች ልጅነቷን ስታስታውስ::

ነገር ግን ጸሃይ እዛ የመማር እድልን ያገኘችው ለሁለት ዓመት ብቻ ነበር:: አሁንም በቤተሰቦቿ ፍላጎት ደጃዝማች አባ ነፍሶ ወደሚባል ትምህርት ቤት እንድትዘዋወር ሆነ::

ምንም እንኳን ጨዋታ ብትወድም ቤተሰቦቿ ለትምህርት ልዩ ትኩረትን የሚሰጡ በመሆናቸው ትምህርትን ማጥናትና ውጤታማ መሆን ግዴታ እንደነበር ነው ጸሃይ የምትናገረው::

"......ያደኩበት ቤት የድሮ ስርዓት ያለበት ቤት ነው:: የአክስቴ ባል አባቴ ተፈረደኝ ነጋዴ ነበር፤ ጥሩ ኑሮ ስለነበረውም ሁሉንም ነገር በስነስርዓት ነበር የሚመራው፡፡ በልጅ አስተዳደግም በኩል ጥብቅ ስነስርዓት ነበር፤ ማስቸገር የሚባለውን ነገር ባናስበው ነው የሚሻለው፤ ሁሉ ነገር ስነስርዓት አለው:: እኔም በተለይም በትምህርቴ ጥሩ የምባል ነበርኩ:: አባቴ ተፈረደኝ የእድሮች ዳኛ አስተባባሪ ስለሆነ የእድሮቹን ሂሳብ መደመር መቀነስ፤ ድግስ ሲኖር የጥሪ ካርዶች ላይ የሰዎችን ስም የመመዝገብ ኃላፊነቱ የእኔ ነበር፤ እኔም ኃላፊነት ይሰማኝ ነበር" ትላለች::

በተለይም አባቷ የሚያሰሯት የሂሳብ ስራ በትምህርት ቤት የሂሳብ ትምህርቷ ላይም ላቅ ያለ ውጤት እንድታመጣ ከሌሎቹ ተማሪዎች ተለይታ እንድትታይ ያደረጋት ከመሆኑም በላይ አምስተኛ ክፍል እያለች የሂሳብ መምህሯን ሂሳብ ልጆቹን በማስተማር ትረዳቸው እንደነበርም ትናገራለች:: ይህ ሁኔታ ደግሞ በስድስተኛም ሆነ በስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ላይ ከፍ ያለ ውጤትን እንድታመጣም አግዟታል::

ጸሃይ አንደኛ ደረጃን አጠናቃ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪ ስትሆን ግን ነገሮች ተቀየሩ፤ እንደውም ተማሪ ሆና መቀጠልም የማትችልበት የህይወት አጋጣሚ ተፈጠረ:: ዘጠነኛ ክፍል ላይ ወደ ትዳርም ገባች::

"......አምስተኛ ክፍል ተማሪ እንዳለሁ የመሬት ላራሹ ጉዳይ ጭቅጭቅ እያስነሳ አንዳንድ ነገሮችም መፈጠር ጀምረው ነበር፤ በዚህ ደግሞ ምኑም ባይገባንም እኛም የችግሩ አንድ አካል ሆነን ፖሊስ እየመጣ ይደበድበን ነበር፡፡ የስምንተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ተፈተንን፤ ጥሩ ውጤት አመጥቼም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ለመቀጠል ልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባሁ:: ነገር ግን ትምህርቱን መቀጠል አልቻልኩም፤ በየቀኑ ፖሊስ ዱላ ይዞ መጥቶ ይደበድበናል:: እቤት ስንሄድ ደግሞ ቤተሰቦቻችን ለምን አርፋችሁ አትማሩም በማለት ይቀበሉናል:: በዚህ ሁኔታ እንዳለን መከላከያ ሚኒስቴር ሴት ወታደሮችን እቀጥራለሁ ብሎ ማስታወቂያ አወጣ:: እኛም ተያይዘን ሄደን ተመዘገብን " ትላለች::

ጸሃይ በጣም ስለምትወደው የወታደርነት መያዋ አውርታ አትጠግብም "...ወታደርነት ሙያዬ በጣም የምወደው ስራዬ ነው፤ ዘጠነኛ ክፍልን እየተማርን በመካከል አቋርጠን ነው ወደ ውትድርና ስልጠና የገባነው " ትላለች::

ምንም እንኳን ወታደር ሲመለመል የሚሄደው ወደፊቼ ማሰልጠኛ ጣቢያ ቢሆንም ጸሀይና ጓደኞቿ ሴቶች ስለሆኑ ልዩ ጥንቃቄና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል ተብሎ ምንም ዓይነት ወንድ ሳይቀላቀላቸው በሆለታ የሚኒሊክ ቤተመንግስት ውስጥ ለአንድ አመት ያህል ስልጠና ወሰዱ::

"......የወታደር ቤት ቆይታዬ ራሱን የቻለ ትልቅ ህይወት ነው:: የሚገርመው ነገር ወታደር ቤት የሄድኩት በትምህርት ቤት የሚደርስብንን ድብደባ ለመዳን እቤትም ለምን አርፋችሁ አትማሩም የሚለውን የቤተሰብ ጭቅጭቅ በመሸሽ ነበር፡፡ ነገር ግን ትልቅ የህይወት ትምህርት ያገኘሁበት እጅግ በጣም አስደሳች ጊዜን የኖርኩበት በጠቅላላው በጣም የምወደው ጊዜ ነበር" ትላለች::

"....እኔና ጓደኞቼ የሰለጠነው ሙሉውን የውትድርና ስልጠናን ነው:: ከግራ ቀኝ እርምጃው ጀምሮ መሳሪያ አነጣጥሮ እስከመተኮስ ድረስ " ትላለች::

የሚገርመው ነገር ደግሞ ጸሀይ በወታደር ቤት የነበራት ቅልጥፍና፣ ተግባቦት፣ ለስልጠናው ያላት ተሳትፎና ጎበዝነቷ ታክሎበት በአንድ አመት የስልጠና ቆይታዋ 13 እና 14 ጊዜ በኃላፊነት ተሹማለች:: በዚህ ሹመትም ጠዋት ተነስታ ጦሩን መቀስቀስ፤ ወደ ቁርስ እንዲሄዱ ማድረግ ከዛም ሰልፍ ሜዳ ሄደው ተቆጥረው ወደስልጠና እንዲሄዱ ታደርግ ነበር:: ይህ ሁኔታ ደግሞ በህይወቴ የማልረሳው እጅግ በጣምም የምወደው የህይወት ጊዜዬ ነው በማለት ትገልጻዋለች::

በዚህ ተሳትፎዋ ደግሞ አለቆቻቸው የሴት ሰራዊት ይቋቋማልና ጎበዞች ይመረጡ በሚባልበት ጊዜም ጸሃይ ከ62 ሰልጣኞች መካከል ከተመረጡት 13 ሴቶች ግንባር ቀደም በመሆን ተመርጣም ነበር::

".....አዎ ሴት ሰራዊት እናቋቁማለን በማለት ጎበዞች ይመረጡ ተባለ፡፡ በዚህን ጊዜ 13 ሴቶች ሲመረጡ አንዷ ሆንኩኝ:: እኛን ደግሞ ለሚቋቋመው ሰራዊት በማስተባበር ሌሎችን ነገሮች ያግዛሉ በማለት ከእስራኤል አገር በመጣች ሴት ሻምበል ልዩ የሆነ ስልጠናን እንድንወስድ ተደረገ፤ ይህች አሰልጣኝ ከሰጠችን ስልጠና ወይንም ደግሞ ስትነግረን ከነበረው ነገር የማልረሳው " እናንተ እድለኞች ናችሁ፡፡ ውትድርና የተቀጠራችሁት ወይንም ደግሞ እየሰለጠናችሁ ያላችሁት አገራችሁን ልታገለግሉ ከጠላት ልትጠብቁ ነው፤ እኛ ግን አገር የለንም፤ አገር ለማግኘት ነው የምንሰለጥነው፤ የምንዋጋው " ትለን ነበር በማለት ታስታውሳለች::

ወታደር ቤት ሆና የነበራት ተሳትፎ ላቅ ያለ ነበር፤ በተለይ ምርቃታቸው ሊደርስ ሲል ኮሚቴ ተዋቀረ አንዱ ስራ የነበረው ለጦሩ ገቢ ማሰባሰቢያ የሚሆን ቲያትር መስራት ነበር:: ጸሃይ ከትምህርት ቤት ጓደኞቿ ጋር ወደጦር ካምፑ እንደመግባቷ ጓደኞቿ ትምህርት ቤት ሆነው ለበዓላት ጊዜ የተለያዩ የስነ ጽሁፍ ስራዎችን እየሰራች ስታቀርብ ያውቋታልና የቲያትሩን ክፍል ጸሀይ ትያዝ አሉ፡፡ ሁሉም በሃሳቡ በመስማማታቸው ጸሀይ ለገቢ ማሰባሰቢያ የሚሆነውን ቲያትር የማዘጋጀት ኃላፊነትን ወሰደች::

"......አዎ ቲያትር አዘጋጂ ሲሉኝ ትንሽ ግር አለኝ፤ ምን ላቀርብ እችላለሁ ብዬም አሰብኩ፤ ነገር ግን የ7ተኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ አንድ ድርሰት ጽፌ ነበር፤ እሱም ቤተሰቦቼ ቤት አስቀምጬ ነው የመጣሁት፡፡ እናም ሳስብ እሱን ድርሰት ለምን ቲያትር አላደርገውም አልኩና ሄጄ ጽሁፉን አመጣሁ፡ ፡ የምፈልጋቸውን ልጆችም ከሰልጣኞች መካከል መረጥኩና ያዝኩ:: ጽሁፉንም ለአለቃዬ አሳየሁ እሳቸውም ወደዱትና መቀጠል ትችያለሽ አሉኝ:: የሚገርመው ነገር ቲያትሩን ለመተወን ሁለት ወንዶች ያስፈልጉ ነበር፤ እኛ መካከል ደግሞ ወንድ እንዳይገባ ሆኖ ብቻችንን ነው እንድንሰለጥን የተደረገው፤ እናም ምን እናድርግ በቃ አንዱን የወንድ ክፍል እኔ ልተውን ሌላውን ደግሞ ጓደኛዬ ልትይዘው ተስማምተን ወደ ልምምድ ገባን" ትላለች::



በጣም የሚገርመው ነገር ግን ጸሃይ በልጅነት አእምሮዋ የደረሰችውና በኋላም ቲያትር ሆኖ እንዲታይ የተመረጠው ድርሰት በጦር ቤቱ ብቻ ተወስኖ አልቀረም:: የሆለታ ከተማ ሙሉውን ማለት ይቻላል ደራሲ ጸሃይ ተፈረደኝ የሰራችው እየተባለ በየምሰሶው በሰዎች አጥር ላይ በባህር ዛፎች ላይ ሳይቀር ተለጥፎ ማስታወቂያ ተሰራለት:: ከዛም መጀመሪያ ጦሩ፣ በመቀጠል ተማሪዎች፣ ኋላም ህዝቡ እንዲያይ ሆነ:: በዚህም ጥሩ ገንዘብ ተሰበሰበ፤ ምርቃታቸውም በጥሩ ሁኔታ ተደግሶ መበላቱን ታስታውሳለች::

ጸሃይና ጓደኞቿ እድለኛም ናቸው ማለት ይቻላል ምክንያቱ ደግሞ ምርቃታቸው የተከናወነው በግርማዊ ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ በመሆኑ::

"...... ጃንሆይ ወታደር መርቀው አያውቁም፤ በወቅቱ ግን የጦር ኦፊሰሮች ስልጠናቸውን አጠናቀው ለምርቃት ተዘጋጅተው ነበር፤ እንደአጋጣሚ ሆኖ እኛም ስልጠናችንን ከእነሱ እኩል ጨረስን፤ በዘህ ምክንያት ጃንሆይ ኦፊሰሮቹን እንጂ ወታደሮቹን አይመርቁም ተባለ፤ የትምህርት ቤቱ አዛዥ ግን እነዚህ ልጆች እድላቸው ነው ለምንድነው አብረው የማይመርቁት ብለው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ጃንሆይን አናገሯቸው፤ እሳቸውም እመርቃቸዋለሁ አሉ"::

"....ጃንሆይ እነዚህን ወታደሮች እመርቃቸዋለሁ ብለው ለመፍቀዳቸው ዋናው ምክንያት በወቅቱ እሳቸው ሆለታ አካባቢ ያሉ ቤተክርስቲያኖች ሲነግሱ በተደጋጋሚ ወደ አካባቢው ይመጡ ነበር እኛ ደግሞ መኪናቸውን አጅበን "ጠቅል ምናለ፤ አገሬን ለሰው አልሰጥም አለ፤ እያልን እየዘመርን እያወደስን እያሞገስን እንሸኛቸዋለን:: እሳቸውም እኮ ግን ባዶ እጃቸውን አልነበረም የሚመጡት በትልቅ የእንጨት አገልግል ፍትፍት፣ ጠጅ ቁርጥ ይዘው ነው የሚመጡት፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ መምጫቸው በጣም ይናፈቅ ነበር" በማለት ወደኋላ በመሄድ ትዝታዋን ትናገራለች::

".....እንግዲህ በዚህ ሁኔታ እኔም ከእሳቸው እጅ ነው ሰርተፍኬቴን ተቀብዬ የተመረኩት:: ይህ ለእኔ እጅግ በጣም ውድና ትልቅ እንዲሁም እድሜዬን ሙሉ የምደሰትበት ታሪኬ ነው" ትላለች::

ከምርቃት በኋላ ምድር ጦርን በ 29 ብር የወር ደመወዝ እንድትቀላቀል ሆነ:: " ....29 ብር በጣም ብዙ ነበር:: ከላዩ ላይ 6 ብር እቁብ ይጣላል፤ 3 ብር የምግብ ማጣፈጫ ተብሎ ይገዛል፤ ሌላው ደግሞ ይለበስበታል " ትላለች::

ኋላ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወደስራው ሲገቡ ደመወዛቸውም ወደ 120 ብር ከፍ አለ፤ ነገር ግን እነሱ ስራ ላይ ሆነው ስድስት ወር እንኳን ሳያስቆጥሩ ጃንሆይ ከስልጣናቸው በሃይል ተገለበጡ:: በዚህ ጊዜ ሁሉም ፊቱን ወደእነሱ በማዞር " ወታደር አትመርቁ ስንላቸው እነዚህን ሚርተኛ ሴት ወታደሮች መርቀው ከስልጣናቸው ተገለበጡ መባል ተጀመረ"፤ በማለት ታስታውሳለች::

ጃንሆይ ከስልጣናቸው ከመነሳታቸው በፊት ግን "....አንድ ቀን ስብሰባ ተደርጎ የማዕረግ አሰጣጥ ይነገራል፤ እናም ጀነራል፣ ሌተናል ጄኔራል የሚኮነው ሰልጥኖ ሰርቶ ብዙ ዋጋ ከፍሎ ተወዳድሮ ነው ይላሉ፤ ነገር ግን የጃንሆይ ማዕረግ የተለየ ነው ማንም አይደርስበትም ይላሉ:: ከዛም እኔ እጄን አወጣሁና እሳቸው ግን የት ተምረው? ከማን ጋር ተወዳድረው ነው? የመጨረሻው ማዕረግ ላይ የደረሱት ብዬ ጠየኩ:: ሁሉም ደነገጡ በድፍረቴም የሚያረጉኝ ነገር አጡ:: በወቅቱ ግን እኔ እውነቴን የተሰማኝን ነበር የተናገርኩት:: ከዛም በቃ ለእኔም መልስ ሳይሰጡኝ ስብሰባው ተበተነ " በማለት ወደትልቁ የህይወት መንገዷ ያስገባትን አጋጣሚ ትናገራለች::

ይህ አጋጣሚ ደግሞ በአለቆቿ እንዲሁም በሌሎቹ ዘንድም ደፋር ያስባላት፣ የብዙዎችን ቀልብ እንድትስብ ሁሉም ለእኔ ለእኔ እንዲል ያደረገ ሆነ:: ነገር ግን አየር ወለድ የነበረውና በሶማሌ ጦርነት ወቅት ከአየር ሲወርድ ጉዳት ደርሶበት በሌላ ስራ ላይ የነበረው አቶ ብርሃነ ገብረመስቀል

**ማህበራዊ**

# የሕይወት ገጽታ

ግን ይህችን ጀግና ሴት የእኔ ካላደረኩ እሞታለሁ አለ።

እህል ውሃ ወይም የእሱ ጥንካሬ ታክሎበት ጸሀይም ጥያቄውን በአዎንታ በመቀበሏ ጀግናዋና ተግባቢዋን ጸሀይን የራሱ የግሉ ማድረግ ቻለ። ብዙም ሳይቆዩ ተጋቡ።

"......ያደኩት በጣም ሴትነት ከሞላበት፤ ሴቶቹ ብዙ ነገር ከሚሰሩበት፣ የሚፈጩበት የሚወቅጡበት በጠቅላላው እረፍት የሌለበት ቤት ውስጥ ነው፤ በዚህ ምክንያት ደግሞ ትዳር ብዙም አስቸጋሪ አልሆነብኝም፤ ካገባሁ በኋላ የማልረሳው የእኔንም የባሌንም ደመወዝ ይዤ ለመጀመሪያ ጊዜ ገበያ ወጣሁ፤ እናም ገበያው ያፈራውን ነገር በሙሉ በያዝኳት ብር ገዛሁ፤ መጨረሻ ላይ ግን 25 ሳንቲም ለታክሲ አጣሁ፤ በጣም ደነገጥኩና ቆም ብዬ ሳስብ ለመጨረሻ ጊዜ የገዛሁት እርድ ነው በቃ ይህንን እርድ መልሱልኝ ልበልና ለታክሲ ላግኝ ብዬ ወደሸጡልኝ አሮጊት ሄድኩና እማማ እባክዎ እርድ ገዝቼ ነበር ግን አሁን ለታክሲ ጨረስኩ እናም እርዱን መልሱልኝና ሳንቲሟን ስጡኝ? ስላቸው በጣም አዝነው እርዱን ተቀብለውኝ ሳንቲሙንና ትንሽ እርድ ሰጥተውኝ በይ ለሌላ ጊዜ ብቻሽን ገበያ እንዳትመጪ ብለው ሸኙኝ" በማለት የትዳር ገጠመኟን ትናገራለች።

ከዛ በኋላ ግን ባለቤቷም እየረዳት ብዙ ነገሮችን አብረው እያደረጉ እየወሰኑ ቀጠሉ" ድሮ እኮ ጎረቤት ዘመድ፣ ቤተሰብ መንገድ ያሳያል፣ ያግዛል። እኔ ትዳር ይዤ ስወጣ የገባሁበት ግቢ ብዙ ሰው ነበር፡፡ ሁሉም እኔን ለማገዝ እርስ በእርሳችን ለመረዳዳት ምንም ምክንያት አንጠብቅም ነበር በጣም የሚገርም ፍቅርና ቤተሰባዊ ሁኔታም ነበረን " በማለት ስለጎረቤቶቿ ትገልጻለች።

ጸሃይ ትዳር ይዛ ከአመት በኋላ የመጀመሪያ ልጇን ወለደች፤ ከዛም አከታትላ አምስት ልጆችን በመውለድ እንዲሁም ስድስተኛ ልጅ በማሳደግ ቤተሰቧን አበዛች። አሁን ላይ ሁሉም በትልልቅ የስራ ኃላፊነቶች ውስጥ ያሉ ከመሆኑም በላይ የልጅ ልጅም ለማየት በቅታለች።

ጸሃይ ልጆቿን እየወለደች ትማር ነበር፡፡ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ከወሰደች በኋላ ግን ወደ ትምህርት ሳትመለስ ረጅም አመትን ለመቆየት ተገደደች። ነገር ግን መማር ህልሟ ነበርና ሁሌም ታስባለች። በመካከልም ንግድ ስራ ኮሌጅ ገብታ በሴክሬቴሪያል ሳይንስ በሰርተፍኬት ተመርቃለች። የጸሃይ ግቧ ግን እሱ አልነበረም። ብዙ መማር ትፈልጋለች።

በ12 ተኛ ክፍል ትምህርት ውጤቷን እንደያዘች የጀመረችው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጋዜጠኝነት እንደቀጠለ ነው። ግን በ12ኛ ክፍል እንዴት ወደጋዜጠኝነት ገባሽ አልኳት" አዎ እኔ 12ተኛ ክፍል ነኝ። ከጦር ሃይሎች ሬዲዮ ከወታደር ቤት ነው ፕሮግራም አርታኢ ሆኜ ኢትዮጵያ ሬድዮ የገባሁት። በሙያዋ ጎበዝ ነች ተብዬም ዲግሪ ካላቸው በላይ ሆኜ የተመደብኩት። ደመወዛችንም ትልቅ ልዩነት ነበረው፤ በዚህም መስሪያ ቤቴ በስራዬ አምኖ እኔን እዚህ ቦታ ላይ ካደረሰኝ እኔ ደግሞ ራሴን አብቅቼ መገኘት አለብኝ በማለትም ነው ወደ ትምህርቱ የገባሁት" ትላለች ።

".....በጋዜጠኝነት ላይ የተማረና ያልተማረ የሚለው ነገር በጣም ያስቸግራል። የመጀመሪያ ዲግሪም ይሁን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ይዘው ተሰጥዖ ስለሌላቸው ውጤታማ መሆን የሚሳናቸው ብዙ ናቸው። ኢትዮጵያ ሬዲዮም የገጠመው ይኸው ነበር፤ እናም ትምህርት ባይኖራቸውም መጻፍ የሚችሉ ድምጻቸው የሚያምር ሰዎችን እንድንቀጥር ይፈቀድልን? ብለው ጠይቀው ለአንድ ጊዜ ብቻ ተፈቅዶላቸው ነው የቀጠሩን። እኔም ጥሩ ቦታ አግኝቼ ነው ስራውን የጀመርኩት" ትላለች።

ነገር ግን ተሰጥዖው ቢኖራትም በስራዋ ላይ የምታጎለው ነገር ባይገኝባትም ከባለዲግሪዎቹ ጋር ግን መስራት በጣም ፈታኝ ሆኖባት ነበር። እንደውም አንዴ የማስታውሰው ትላለች "አንዱ ዲግሪ ያለው ወጣት ስራ ይዞ መጣ፤ እኔም አየሁትና በዚህ በዚህ መልኩ አስተካክለው ስለው በጣም ተናዶ" እንኳን መሀይም ልጆችም ቢያዙኝ እሰራለሁ" ብሎ ሄደ "።

ይህ ሁኔታ ደግሞ መማር እንዳለባት አመላከታት እንጂ አልችልም ብላ እንድትቆም አላደረጋትም። ይህንን የተናገራትን ሰው አሁንም ታመሰግነዋለች። ምክንያቱም ንግግሩ በትምህርቷ ለመግፋቷ መንገዱን ስላሳያት።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች ግን" ማስ ሚዲያ ትሬኒንግ ኢንስቲትዩት" የሚባል የጋዜጠኝነትን ትምህርት አስተምሮ በዲፕሎማ የሚያስመርቅ ተቋም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ተከፈተ። የመጀመሪያው ዙር ስለሁኔታው ሳትረዳ ምዝገባው አለፋት ። ጸሀይ በዚህ ከፍተኛ ቁጭት ውስጥ ገብታ እንዳለች ግን የስራ ባልደረቦቿ "ለምን አትማሪም የሚል ጥያቄ አቀረቡላት " የእሷም መልስ "ለምን አልማርም መማር እችላለሁ" የሚል ሆነ። ይህንን የተረዳችው የስራ ባልደረባዋና ጓደኛዋ ሰሎሜ ደስታም ስብሰባ ላይ ሀሳቡን



አቀረበች። ኮሚቴ ሆነው የተቀመጡት ግን "እሷ የልጆች እናት አይደለች እንዴት ብላ ነው የምትማረው" አሉ። በዚህን ጊዜ ጓደኛዋ የልጆች እናት ብትሆንም እማራለሁ ብላለች እድል ይሰጣት አለች በቃ ትወዳደርና ትማር ብለው ወሰኑ።

".....ጓደኛዬ ስብሰባ ላይ ባቀረበችው መሰረት ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ሂጂና ተወዳደሪ አሉኝ። እኔም እሺ ብዬ ወደ ውድድሩ ቦታ ስሄድ የ12ኛ ክፍል ውጤቴን ሲያዩት ከሚፈልጉት መግቢያ ነጥብ በላይ ነው በቃ አንቺማ አትወዳደሪም ዝም ብለሽ ግቢ አሉኝ፤ በቃ አልፌ ገባሁ" ትላለች።

ቁጭ ብላ ትምህርት ቤት መግባቷን ስታስብ በሁለት ነገሮች መወጠሯን ታስታውሳለች አንዱ እንዴት ብዬ ነው ውጤታማ የምሆነው ሲሆን ሌላው ደግሞ ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ ትምህርት ቤት መግባት መቻሌ እድለኛ ነኝ የሚል ነበር።

".....ትምህርት ተጀመረ፡፡ እኔም ተማሪ ሆንኩ ከዛ የመጀመሪያ የእንግሊዘኛ የሙከራ ፈተና ተፈተንኩ። እኔም በሞራል በደስታ ፈተናውን ሰራሁት፤ በሁለተኛው ቀን ውጤቱ ሲመጣ ግን በጣም አስደንጋጭ ሆነ፡፡ ከሃያው ያገኘሁት " ዜሮ" ነበር። መቼም ድንጋጤዬ ድንጋጤ አይደለም ወረቀቱን እጥፍጥፍ አድርጌ ለማንም ሳላሳይ እንደውም 15 ከሃያ አገኘው እያልኩ ጓደኞቼን እየዋሸሁ እያለቀስኩ ወደ ቤቴ ሄድኩ " በማለት ታስታውሰዋለች።

በለቅሶ ብዛት እራሷን አሟትና ደክሟት የተኛችውን ጸሃይ የመጀመሪያ ልጇ ከትምህርት ቤት ስትመጣ እናቷ ተኝታለች። ምን እንደሆነች ብትጠይቅም የሚነግራት አላገኘችም። ከዛም የተኛችውን እናቷን ቀስቅሳ ምን እንደሆነች ስትጠይቃት ለማንም እንዳትናገሪ በማለት የተፈጠረውን አሳየቻት። ልጇም ቁጭ ብላ ፈተናውን ስታየው እናቷ የተሳሳተችው ምን እንደሆነ ገባት። ስህተቷን አሳይታ ምን ማድረግ እንደነበረባት ነግራ ከዚያ በኋላም በሁሉም ነገር እንደምትረዳት ቃል ገብታ አጽናናቻት።

"......ልጄ ፈተናውን ስታየው አልደነገጠችም፡፡ እንደውም ስህተቴን ቁጭ ብላ በማየት ነገረችኝ ማድረግ ስለነበረብኝ ነገር አብራራችልኝ፤ ስህተቴም ትዕዛዝ አለማንበቤ መሆኑ አወቅሁ፤ ከዛ በኋላ እኔ አለሁ አለችኝ። ለወንድሟም ነግራው እሱም እናቴ እኔም እረዳሻለሁ ቀጥይ አለኝ፤ ከዛ በኋላ የቤት ስራ ሲኖርብኝ እነሱ እያሳዩኝ ከእነሱ ጋር መስራት ጀመርኩ፡፡ በኋላም እኔም እየገባኝ በደንብ ወደትምህርቱ እየገባሁ መጣሁ። ያ በዜሮ የተጀመረው ትምህርት በማዕረግ በመመረቅ ተጠናቀቀ " ትላለች።

ጸሃይ ማንም ሰው በትክክል ችግሩን ተናግሮ እርዳታ ከፈለገና በዛ ልክ የሚረዳው እንዲሁም የሚረዳው ካገኘ ያሰበበት ይደርሳል። ይህ ደግሞ በእኔ ህይወት አይቼዋለሁ ትላለች።

በዚህ ሞራል የተጀመረው ትምህርትም አሁን መስመር ይዟል። ጸሀይ ዲፕሎማዋን እንደያዘች ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ የዲግሪ ፕሮግራም በመጀመሩ እዛው ቀጠለች። ለዚህ ሁሉ ነገር ግን ልጇ ያበረከተችውን አስተዋጽዖ ደጋግማ ትናገራለች። ታመሰግናታለችም። ጸሃይ በዚህ አላበቃችም፡፡ ከጡረታ በኋላ ሁለተኛ ዲግሪዋን በመማር የትምህርት ጥማቷን ተወጥታዋለች።

ኢትዮጵያ ሬዲዮ ላይ እረፍት የለሽ ስራ ነበር የምንሰራው የምትለው ጸሃይ በሳምንት ሁለትና ሶስት ፕሮግራሞችን አየር ላይ ማዋል። በሳምንት ሁለት ጊዜ ፕሮግራም መሪ መሆን፤ የመስክ ስራ መሄድ፤ የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን አዳምጦና አርትኦት ሰርቶ ይለፍ ብሎ መፈረም፤ የተለያዩ ድራማዎችንም ይዘታቸውን ማየትና ማረም ብቻ ጥሩ ነበር በማለት ታስታውሰዋለች።

".....በህይወት ዙሪያ የሚል ፕሮግራም ነበረኝ፤ በዚህም ሴቶችን ህጻናትን ገጠር ከተማውን የሚመለከት ነበር። እዛ ላይ የሰራሁትን ስራ ምንጊዜም ቢሆን አልረሳውም፤ እወደዋለሁ፤ ኢትዮጵያን እንቃኛት የሚል ፕሮግራምም ነበር፤" ትላለች

ሁሉም ስራዎቿ የመስክ ጉዞን የሚፈልጉት ጸሀይ የምታደርገው ነገር አንዴ መስክ ከወጣች ብዙ ጊዜ ትቆያለች በዚህ ቆይታዋ ደግሞ ለሴቶች ፕሮግራም፣ ለኢትዮጵያን እንቃኛት እንዲሁም ሌሎች በመንገዱ ያገኛቻቸውን ለፕሮግራም ይመጥናሉ የምትላቸውን በሙሉ ነው ሰብስባ የምትመጣው።

ጸሃይ በስራዋ እጅግ በጣም ታታሪ ናት፤ ይህንን ደግሞ ብዙ ጓደኞቿም እንዲሁም ስራዋም ይመሰክራሉ".... የሚገርመው ነገር ልጆቼን ባሌን ትቼ ረዘም ያለ የመስክ ስራ እሄዳለሁ፤ ለስራው በጣም ራሴን ከመስጠቴ የተነሳ ክልል ላይ ለመሄድ ሳስብ የተቋሙ መኪና እስኪዘጋጅ እንኳን አልታገስም፤ ራሴ ትኬቴን ቆርጬ ከህዝብ ጋር ጉዞ አደርጋለሁ፤ ይህንን አሁን ላይ ሳስበው በጣም ይገርመኛል" በማለት ወደኋላ ሄዳ የስራ ጊዜዋን ታስታውሳለች።

በጋዜጠኝነት ህይወቷ ከማትረሳቸው በርካታ ገጠመኞቿ አንዱን ስትናገር " አንድ ጊዜ ከእንግሊዝ አገር ልዕልት አን መጣች፤ እዚህ ከደረሰች በኋላ የሚያጅባት ሰው ስለጠፋ አንድ ሴት ጋዜጠኛ ላኩ ይባላል፤ ስራ አስኪያጁ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ይጠራኝና 10፡30 ላይ ኡጋዴን ስለምትሄጂ አሁን አድርሶ የሚመልስሽ መኪና ተዘጋጅቷል ቤትሽ ሄደሽ ልብስሽን ይዘሽ ነይ፤ አሉኝ፤ በጣም ደንግጬ እሺ ብዬ ወደቤቴ ሄድኩ ልጆቼ ትምህርት ቤት ናቸው፤ ባለቤቴ ስራ ነው፤ ማንም ማግኘት አልችልም፤ እንደ አሁኑ የእጅ ስልክ (ሞባይል) የለም በቃ እቤት ላለችው አጋዤ የት እንደምሄድ ነግሬያት ቻው ብዬ ወጣሁ፤ 15 ቀን ያህል አልተመለስኩም። ይህ የማልረሳው የመስክ ስራዬ ነው" በማለት ያለፈችበትን ከባድ ጊዜ ታስታውሳለች።

እንደዚህ አይነቱን ወታደራዊ ትዕዛዝ እኮ ያኔም አሁንም ማንም እሺ አይልም፤ ነገር ግን በእኔ ውስጥ የተለየ የሙያ ፍቅርና ክብር ስለነበረኝ ህጻናት ልጆቼን እንኳን ትቼ ስዘምት ነው የኖርኩት በማለት ትናገራለች።

ነገር ግን ብዙ ከለፋችበት ብዙም ልትሰራ እቅድ ካደረገችበት መስሪያ ቤት የ 1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በተፈጠሩ ምቹ ያልሆኑ የስራ ሁኔታዎች ምክንያት ለመቀጠል ባለመቻሏ ጡረታዬ ሲደርስ አስከብራለሁ ብላ በፍቃዷ ስራዋን ስለመልቀቋ ትናገራለች።

ብዙ የሚያስገርሙ ነገሮችን እያወራን መጥተናል ግን ለአንቺ በህይወትሽ ትልቅ የምትይው አስገራሚ ክስተት ምንድነው ? ብዬ ለጠየኳት ስትመልስ ፤ "..... በህይወቴ ብዙ የሚያስገርሙ ነገሮችን አልፌያለሁ። ነገር ግን ልፋቴን ድካሜን ፈጣሪ ቆጥሮት ነው መሰለኝ ኢቢሲን በለቀቅሁ በ15 ዓመቴ ለሽልማት መጠራቴ በጣም ይገርመኛል። በወቅቱ እንደምሸለምም አላውቅም የጠሩኝም ጓደኞቼ ናቸው። እናም በዚህ በጣም እደሰታለሁ" ትላለች።

ጸሃይ በስራዋ ኢትዮጵያን ከጫፍ እስከ ጫፍ ቃኝታ አስቃኝታናለች፤ "አገሬ ውብ ናት ከእኛ የመስራት አቅም በላይ የሆነች ናት፤ ምንም አልሰራንም እዚሁ አዲስ አበባን ከበን ነው ያለነው፤ ወጣ ሲባል በጣም የሚገርም መልከዓ ምድር ያላት ናት፤ ህዝባችንን ለስራ ማሰማራት ብንችል ከእኛ በላይ ሀብታም አይኖርም። ግን ይኸው እስከ አሁንም እየተራብንና እየተቸገርን ነው፤ ብዙ ማሰብም ብዙ መስራትም ይጠበቅብናል" ትላለች። ጸሀይ ከኢትዮጵያ ውጪም ኬኒያ፣ ጋና፣ ግብጽና ስዊዲን ሄዳለች።

በጋዜጠኝነት ህይወትሽ አልሰራሁትም ብለሽ የምትቆጪው ነገር አለሽ? ስላት".....አይ አልሰራሁትም ሳይሆን መቀጠል ሲገባኝ አለቦታው ስራዬን አቆምኩት። እንደውም ልጆቼ እያደጉ የሚጎትተኝ ነገር እየቀነሰ ስጋቶቼ ሁሉ ተቃለው ስራዬን ሰፋ አድርጌ ልሰራ በምችልበት ጊዜ ማቆሜ በጣም ይቆጨኛል፤ ኢትዮጵያን ለትውልዱ ማስጎብኘት አለመቻሌ እስከ አሁን ይቆጨኛል፤ " በማለት ትናገራለች።

ዛሬ ላይ የምንወቅሰው የምንከሰው ትላንት ያልፈጠርነውን ወጣት ነው፤ ወጣቱ ለረጅም ዓመታት በሚባል መልኩ ተመልካች አጥቷል፤ ወላጅ እንዳይዝ የሚጎትተው ነገር ብዙ ነው፤ በመሆኑም ትውልዱን እናስተምር ልምዳችንን እናካፍል በጎውን መንገድ እንምራ በማለት ከጎደኞቼ ጋር ዩቱዩብ ከፍተን ለማስተማር እየተዘጋጀን ነው ትላለች።

ጸሀይ ኢቢሲ ከ 15 ዓመት በኋላ ለሚዲያው ባበረከትሽው አስተዋጽዖ በሚል ሽልማት አበርክቶላታል። ከዛ ተከትሎም "ተወዳጅ ሚዲያ" የሚባል ተቋም ደግሞ እሷ ሳታውቅ ከልጆቿ ጋር በመነጋገር "ጸሃይን እናመስግን" በማለት ፕሮግራም አዘጋጅተው እውቅና ሰጥተዋታል፤ በዚህም ትልቅ ደስታና ክብር ይሰማኛል ትላለች።

**መልዕክት**

አሁን ላይ በሙያ ላይ የሚታዩ አንዳንድ አጓጉል ሁኔታዎች አሉ፤ ለምሳሌ ስራውን ራስን ለማውጫ ከሌሎች ጋር በጥቅም ለመወዳጃ የማድረግ ነገር ይታያል። ይህ ደግሞ ሙያውን የማያሳድግ እንደውም የሚገል ሆኖ አገኘዋለሁ። ለምሳሌ አንድ ጋዜጠኛ አንድ ቦታ ላይ ይሄድና በቃ ከዚህ በኋላ እኔ ብቻ ነኝ የምመጣው ሌላ ሰው ቢመጣ መረጃ እንዳትሰጡ ብሎ ዘግቶ ይመጣል፤ ገንዘብ አለ ተብሎ በሚታሰብበት ቦታ ላይ ራስንና ሙያውን አዋርዶ መሻማት ይታያል፤ የጋዜጠኝነት ህይወት ደግሞ ፍጹም ይህንን የማይፈልግ ይልቁንም ራስን መስጠት የሚፈልግ ነው። በመሆኑም በሙያው ውስጥ ያሉ ወጣቶች ከጥቅም ይልቅ ለሙያዊ ስነምግባር ታማኝ በመሆን ለህብረተሰቡ አርዓያ መሆን አለባቸው።

# የህብረተሰብ ተኮር ቱሪዝም አዲስ መንገድ

**ዳግም ከበደ**



ሌኮ ሉጆች የቱሪዝም ዘርፋን ብቻ ሳይሆን የቱሪስት መስህቦች ያሉባቸውን አካባቢዎች ማህበረሰብ በመጥቀም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖራቸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽና ሰፊ የባህል ሃብት ካላቸው አገራት ተርታ ትመደባለች። አገሪቱ የሰው ዘር መገኛም ናት፡፡ የብዝሃ ባህልና እምቅ የቱሪዝም ሃብት ባለቤት ከመሆኗ አንፃር ከዘርፉ ብዙ ትጠቀማለች ተብሎ ይጠበቃል። ይሁን እንጂ እንዳላት የተፈጥሮ፣ የታሪክና የብዝሃ ማንነት ሃብት ከቱሪዝም ዘርፍ እዚህ ግባ የሚባል ጥቅም እንዳላገኘች ይገለጻል።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ዓለማችን ላይ በጎብኚዎች መዳረሻነት ከሚታወቁት አገራት ተርታም መሰለፍ አልቻለችም። እነዚህ አገሮች በባህላዊ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ እሴቶቿ በብዙ እጥፍ የምታስከነዳቸው አገራት ሃብቶቻቸውን የመጠበቅ፣ የማስተዋወቅና ምቹ መሰረተ ልማት በመገንባት የመንከባከብ ተግባር በመስራታቸው ብቻ ቱሪዝምን የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽና የጀርባ አጥንት እንዲሆን አስችለውታል።

ወደ አገራችን ስንመጣ ግን ይህ የተገላቢጦሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ "በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል" እንዲሉ አገሪቱ የቱሪዝም ዘርፉን እሴቶች በሚገባ በመረዳት ከዚያም ተጠቃሚ ለመሆን የሚጠበቅባትን ያህል ሳትሰራ ቆይታለች፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን የአገሪቱን የቱሪዝም መስህቦች የጎበኙ የውጭ ቱሪስቶች በደብዛዛውም ቢሆን ስለድንቅ የቱሪዝም ሀብቶቿ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በመደነቅ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ይሰማል። ይህ ነው የሚባል የአገር ውስጥ ጎብኚ ባይኖርም፣ በአገራቸው የቱሪዝም ሃብት ኮርተው ዙሪያ ገባውን በመቃኘት ዓለም ትኩረት እንዲሰጠው የሚሞግቱም የአገር ውስጥ ጎብኚዎች አልጠፉም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መንግስት ዘርፉን በሚገባ መጠቀም የሚያስችሉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

ቱሪዝምና መዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ ጎብኚዎችን በመሳብ እንዲሁም አዳዲስ መዳረሻዎችን በመፍጠር ከሃያላኑ ተርታ የሚያሰልፍ ጠንካራ ኢኮኖሚና እጅግ ተወዳጅ አገርን በመፍጠር ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደሚቻል ታምኖበት እየተሰራ ነው። በአዲስ አበባ የቱሪስቱን ቆይታ ሊያራዝሙ የሚችሉ የግዙፍ ፓርኮች ግንባታዎች ተካሂደዋል፤ በገበታ ለአገር ፕሮጀክት ደግሞ በኮይሻ፣ በወንጪና በጎርጎራ ግዙፍ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው፡፡ መንግስት አገሪቱን ከብልጽግናው ማማ ላይ በክብር ለማስቀመጥ የቱሪዝም ዘርፉን ከኢኮኖሚው ዋና ዋና ምሰሶዎች አንዱ ዘርፍ አርጎ አስቀምጦ እየሰራ ይገኛል።

መንግስት የቱሪዝም መዳረሻዎችን ከማልማት፣ የመስህብ ስፍራዎችን ከማስተዋወቅና መሰል ዘርፉን የሚያንቀሳቅሱ ተግባራት ላይ ከመሳተፍ ባሻገር የግሉ ዘርፍ፣ ባለሃብቶች እና ሌሎች ከቱሪዝም ጋር ተያያዥ ትስስር ካላቸው አካላት ጋር እንዲሰራ ይጠበቃል። በዋናነት በእቅዱ የያዛቸውን ፕሮጀክቶች እነዚህ አካላት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንዲደግፉ በሩን ክፍት ከማድረግ ባሻገር በግል ተነሳሽነት ለአገሪቱ ቱሪዝም የሚጠቅሙ እቅዶችና አዳዲስ ፕሮጀክቶች ሲኖሩ በሙሉ አቅም በመደገፍ እውን እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥር ይጠበቃል።

ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያ ውስጥ በቱሪዝም ዘርፍ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተቀናጅቶ በመስራት በኩል ጎልቶ የሚታይ ሁኔታ እንደሌለ አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። የግሉም ዘርፍ አዳዲስ የቱሪዝም ፅንሰ ሃሳቦችን በማምጣትና በማስፋፋት የድርሻውን ከመወጣት አኳያ እዚህ ግባ የሚባል ስራ ሲከውን እንደማይታይ ይነገራል። በእርግጥ በሆቴልና ሆስፒታሊቲው ዘርፍ የግል ባለሃብቶች የማይናቅ አበርክቶ እንዳላቸው ግን የሚካድ አይሆንም።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የባህልና ቱሪዝም አምዳችን በግል ጥረት ለቱሪዝም ዘርፉ የበኩሉን አበርክቶ ለማኖር የሚጥር የአንድ ግለሰብ ፕሮጀክትን በመዳሰስ ይህን መሰል ጥረቶች በጥቅሉ ስለሚኖራቸው ፋይዳ ይዳስሳል። እግረ መንገዱንም መንግስትና የግሉ ዘርፍ ቅንጅት አስፈላጊነትን በመዳሰስ ለቱሪዝም ዘርፉ ያለውን ፋይዳ አንመለከታለን። ይህ ወጣት በግል ተነሳሽነት በምዕራብ ጎጃም ዞን ደጋ ዳሞት ወረዳ የሚገኘው ማራኪው ሙሉ ኢኮ-ሎጅ መስራችና ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት የቱሪስት መስህብ እንዲሆን ጉልህ ድርሻ መጫወት የቻለ ነው።

### ጥቂት ስለ ሙሉ ኢኮ ሉጅ

ሙሉ ኢኮ ሎጅ በዓይነቱ የተለየ በየትኛውም ሁኔታ ተፈጥሮን ማዕከል አድርጎ የተሰራ እና አገር በቀል እውቀትንና የማህበረሰቡን ወግና ባህል ለሌሎች ማስተዋወቅን እና ተጠቃሚ መሆንን ታሳቢ ያደረገ ነው። የዚህ ሃሳብ ጠንሳሽና ልምድና ዕውቀቱን ለተወለደበት ማህበረሰብ በማካፈል ህዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደረገው ወጣት አብይ ዓለም ኑሮውን በጀርመን አገር ባደረገበት ጊዜ ከቀሰመው ልምድ በመነሳት ሎጅ ማልማት ውስጥ እንደገባ ይገልፃል።

የሙሉ ኢኮ ሎጅ በጮቄ ተራራ አካባቢ ይገኛል። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የጮቄ አካባቢ የመሬት አቀማመጥ 86 ከመቶ ተራራማ 1 ነጥብ 5 ከመቶ ሸለቋማ ና 12 ነጥብ 5 ከመቶ ሜዳማ ነው፡፡ የጮቄ የተፋሰሱ የታችኛው ክፍል ማለትም የአባይ ወንዝ እና መሰል አካባቢዎችን ተከትሎ ሸላቋማ ሲሆን፣ በዚህ አካባቢ እንደ ሾላ፣ ሉል፣ ክትከታ፣ ግራር፣ ቅላባና አምብስ በመሳሰሉ እፅዋቶች የተሸፈነ ነው፡፡ የመካከለኛው ክፍል ተራራማና ተዳፋታማ ሲሆን፣ ይህ አካባቢ በዋናነት በአስታ የተሸፈነና አልፎ አልፎ በአዕምጃና በሌሎች የተሸፈነ ነው፡፡

የጮቄ የላይኛው አካል በአብዛኛው ሜዳማ ሲሆን ይህም በጅብራ፣ ግምይና አሸንግድየ ተክሎች የተሸፈነና አካባቢው ከፍተኛ የሆነ የግጦሽ ጫና ያለበት ነው፡፡ ከጠጠር ወደ ድኋ ፅዮን ሲጓዙ ግምይና ጅባራ የበዛበትን ድልዳላማ መሬት አልፈን የምናገኘው የፍልፈል ሜዳ ከፍተኛ ቦታን እናገኛለን፡፡ ይህ ቦታ ለቱሪስት ማረፊያነት ማገልገል የሚችል ሲሆን የአካባቢውን ገፅታ ለመመልከት የሚያስችል ከፍተኛ ቦታ ነው፡፡

የጮቄ ተራራ ልዩ ውበትና ተፈጥሮአዊ ፀጋ መላበሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የአፍሪካ የውሃ ማማነቱን ሊቀንስ የሚያስችሉ ድርጊቶች ሲፈፀሙበት ይታያል፡፡ ለምሳሌ ልቅ ግጦሽ፣ የደን መጨፍጨፍና ብርቅዬ የዱር እንስሳት መመናመን፣ በአካባቢው ባሉ አርሶ አደሮች በእርሻና በመኖሪያ ቤት መወረር ይታይበታል፡፡ ስለሆነም ቀጣይ ይህንን ቦታ ከነውበቱ ለማስቀጠልና ለማልማት ከመንግስትም ሆነ በየደረጃው ካለው ማህበረሰብ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠውና የልማት ፕሮጀክት ሊነደፍለት እንደሚገባ ባለሙያዎች ምክረ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ፡፡

የሙሉ ኢኮሎጅም ይህንን የአፍሪካ የውሃ ማማ እየተባለ የሚጠራ ቦታን ተጎራብቶ የሚገኝ ነው። የኢኮ ሎጅ መስራቾችና በአካባቢው የሚኖሩ ማህበረሰቦችንም ይህን መሰል መስህብነቱን የሚቀንሱ እንቅስቃሴዎች እንዲገደቡ፣ የቱሪስት መዳረሻነቱ እንዲጨምር፣ ከዚህም በላይ በአገር በቀል እውቀትና በራስ ማንነት ላይ የተመረኮዘ የኑሮ ዘይቤ ቀጣይነት እንዲኖረው እየሰሩ ይገኛሉ። የማህበረሰብ አቀፍ ሎጁ በደብረማርቆስ በደምበጫ በኩል 37 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ ሲሆን፣ ተራራማና ለእይታ እጅግ ማራኪ በሆነ ወደ 3ሺህ 50 ሜትር ከፍታና አቀማመጥ ላይ እንደሚገኝ የኢኮ ሎጁ መስራች አብይ ይናገራል።

እንደ ማህበረሰብ አቀፍ ሎጁ መስራች ገለፃ፤ በአካባቢው ሰፊ የተፈጥሮ፣ የባህልና ያልተበረዘ የአኗኗር ዘይቤ ቢኖርም በሚፈለገው መንገድ የቱሪስት መዳረሻ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ ቆይቷል። እርሱ ኢትዮጵያን ለጎብኚዎች በሚያሳየው "የቱሪስት ጋይድ" ስራ ላይ ተሰማርቶ ስለነበር ያንን አጋጣሚ በመጠቀም ከእምቅ ሃብቱ ነዋሪው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት መቀየስ ችሏል። በዚህም በርካታ ጎብኚዎች በስፍራው እየተገኙ ውብ ተፈጥሮውንና ማራኪ የኑሮ ዘይቤውን ከነዋሪው ጋር በቀጥታ ተገናኝተው እንዲያጣጥሙ እድሉን እንዲያገኙ ማድረግ ችሏል።

"ቱሪዝም አለ ህብረተሰብ ተሳትፎ ዘለቄታ የለውም" የሚለው አብይ አለም፤ በኢኮ ሎጁ በዋናነት ማጉላት የፈተፈለገው ያንን እንደሆነ ይናገራል። በተለይ ከ85 በመቶ በላይ አርሶ አደር የሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ ማሳተፍ ሳይቻል ስለ ቱሪዝም እድገት ማሰብ እንደማይቻል በማንሳትም ይህንን ለማሳካት በሎጁ ጎብኚዎች በሚገኙበት ወቅት የአካባቢው አርሶ አደር ባህሉ የሆነውን ቆሎውን፣ ዳቦውን፣ ባህላዊ መጠጡንና መሰል ከእለት ተእለት ኑሮው ጋር የሚገኘውን ነገር በማቅረብ እንግዶቹን እንዲቀበል ይደረጋል።

በዋናነት ቱሪስቱ የአካባቢው ማህበረሰብ ቱባ ባህል ከራሱ ከአርሶ አደሩ ጋር በቆየበት ጊዜ ሁሉ እንዲኖረው በማድረግ የሚተገበር ማህበረሰብ ተኮር ቱሪዝም እንደሆነም ይናገራል። በተለይ በዚህ ማህበረሰብ አቀፍ ኢኮ ሎጅ ውስጥ ጎብኚዎች የኢትዮጵያውያንን እንግዳ ተቀባይነት እንዲመለከቱ እድሉን ከመፍጠር ባሻገር የገቢ ምንጭ እንዲፈጠርላቸውም የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ይናገራል።

የአካባቢው ማህበረሰብ በሎጁና በዙሪያው ባሉ መኖሪያ አካባቢዎች ከጭቃ፣ ከቀርከሃና ከሳር ክዳን የሚሰሩ የተዋቡ ቤቶችን ጎብኚዎች በቀጥታ በጋራ እንዲሰሩና ልምዱን እንዲካፈሉ በማድረግ ያመቻቻሉ። የድሮ ባህላዊ ቤት አሰራር እንዳይጠፋና የማህበረሰቡ ቱባ የአኗኗር ዘዬ እንዳይበረዝ የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ። ከዚህ ባሻገር በእሳት ዳር ጨዋታ ከሩቅ አገር ለሚመጡ የውጪ አገር ጎብኚዎች የማህበረሰቡን የጨዋታ ወግ፣ ዘፈንና ባህላዊ ውዝዋዜ በማሳየት ከምንም ነገር በላይ ቱሪስቱ ተዝናንቶና በድጋሚ ለመምጣት እቅድ ይዞ እንዲሄድ ለማድረግ እንደሚጥሩም የሎጁ መስራች አቶ አብይ ይናገራል።

"ይህን የመሰለ ውብ የእንግዳ አቀባበል ቱሪስቶች ከተደረገላቸው በኋላ ቀጣይ የሚሄዱት በአካባቢው ነዋሪ ወደሆኑ አርሶ አደር ቤት ነው" የሚለው የኢኮ ሎጁ መስራቹ፣ በዚህም ቱሪስቶቹ አርሶ አደሩ የሚኖረውን የእለት ተእለት ኑሮ በጋራ እንዲካፈሉ ይደረጋሉ። እርሻ ማረስ፣ ማጨድ፣ ከብት ማሰማራት እንጨት መልቀምም ሆነ ማንኛውንም ነዋሪው በየእለቱ የሚያከውናቸውን ተግባራት በቀጥታ ተሳትፎ እንዲከውኑ ይደረጋል። ለቤት መስሪያ ጭቃ ከማቡካት ጀምሮ ለውቂያ የደረሰ እህል እስከ ማበራየት ከጎብኚዎቹ ይጠበቃል።

### ፅንሰ ሃሳቡን ስማስረፅ

የሙሉ ኢኮ ሎጅ ማህበረሰቡንና ጎብኚዎችን በቀጥታ በማገናኘት ቱሪስቱ ማራኪ ቆይታ እንዲያደርግ ከማድረጉም ባሻገር አዲስና በዓይነቱ ለየት ያለ የቱሪዝም ፅንሰ ሃሳብ እንዲተዋወቅ እድሉን ያመቻቸ ነው። ከሁሉም በላይ ግን የማህበረሰቡ ባህል እንዳይበረዝ፣ ወግና ስርአቱን እንዳይለቅ በተለይ ደግሞ እንግዳ ተቀባይነቱን የሚታወቅበትን ማንነቱን እንዳይሸረሸር ትልቅ እገዛ የሚያደርግ ፅንሰ ሃሳብ ነው። ይህ ማህበረሰብ ተኮር የቱሪዝም እንቅስቃሴ ልክ በደቡብ ጎንደር አውራምባ ማህበረሰብ ማህበረሰቡ ጠንካራ የስራ ባህልና ንቁ ዜጎችን ፈጥሮ አካባቢውን ባህሉንና ኑሮውን በእውቀት እንዲመራ እድሉን እየፈጠረ የሚገኝ ነው።

በተለይ መንግስት አዳዲስ የቱሪዝም ዘርፎችን ለማስተዋወቅ፣ መዳረሻ ስፍራዎችን ለማልማት፣ ማህበረሰቡን ያካተተ ቱሪዝምና በዚያ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያደርገውን ጥረት አጋዥ እንደሆነ በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ወቅት ያለ እረፍት ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላኛው ባዝነውና ይህ ነው የሚባል ቁምነገር ሳይጨብጡ ቆይታቸውን ከሚጨርሱ መሰል ስልቶችን በመንደፍ አንድ አካባቢ ላይ በቂ የቆይታ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማድረግ ሎጁ ትልቅ ምሳሌ መሆን የሚችል ነው። በተለይ መሰል የቱሪዝም ፅንሰ ሃሳቦችን በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ማስፋትና ከዚያም ሁሉም ባለድርሻ አካል ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ

**ዋስልኝ አየለ**

ቀኑ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ነበር። ዕለቱ ደግሞ ሰኞ፤ የሳምንቱ የመጀመሪያ የሥራ ቀን። ሥራ የዋለ ሁሉ ወደ ቤቱ ገብቷል፤ እንደየሥራው ባህሪ በሥራ ላይም ያለ ይኖራል።

ሰዓቱ ምሽት 3፡00 አካባቢ ነው። የደከመው ተኝቷል፤ አብዛኛው ሰው ግን ገና ያልተኛ ይመስላል። በድንገት የማህበራዊ ድረ ገጾች ላይ አንድ አስደንጋጭ ዜና መዘዋወር ጀመረ። ይኸውም ‹‹ሃጫሉ ተገደለ›› የሚል ነበር።

በማህበራዊ ድረ ገጾች ሀሰተኛ ዜና ማሰራጨት የተለመደ ነውና ብዙዎች ለማመን ተቸገሩ። አንዳንዶችም ‹‹ኧረ እባካችሁ እንዲህ አይነት ቀልድ አደጋ አለው!›› እያሉ ይመከሩ ነበር። ዳሩ ግን የመረጃዎች ፍጥነት በአንድ ጊዜ ማህበራዊ ድረ ገጾችን አጥለቀለቀው።

አሁን ነገሩ እውነት ይሆናል ተብሎ መጠርጠር ተጀመረ። ወዲያውኑ ፈቃድ ያላቸውና መደበኞቹ መገናኛ ብዙኃን እውነት መሆኑን አረጋገጡ። አሁን ድንጋጤ ተጀመረ! ምክንያቱም ግድያው ፍጹም አስደንጋጭ ነበር።

ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ማህበራዊ ድረ ገጾች፣ በመንግስት እና በፖለቲከኞች የሚተዳደሩት ዋናዎቹ መገናኛ ብዙኃን ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው መረጃዎችን ማሰራጨት ጀመሩ። አሉባልታ እና የብሽሽቅ ስድድቦች በስፋት ተሰራጩ። ከአርቲስቱ ግድያ በላይ ፖለቲካዊ ጭቅጭቆች አየሩን ሞሉት። ግድያው በማን እንደተፈጸመ ግልጽ አልነበረምና የአርቲስቱ ተቆርቋሪ ነን የሚሉ ወገኖች ገዳዮች እነ እገሌ ናቸው የሚል የግምት መረጃዎችን ማሰራጨት ጀመሩ።

እንዲህ እንዲህ እያለ ያ አስደንጋጭ ምሽት ነጋ። ሰዎች ወደ ሥራ ለመሄድ እያመነቱ ነው። ምክንያቱም በማህበራዊ ድረ ገጾችና በዋናዎቹ በጽንፈኞች በሚተዳደሩት መገናኛ ብዙኃን በሚሰራጩ መረጃዎች፣ እንዲሁም ከግድያው ድንገተኛነት አንፃር የፀጥታ ሥጋቶች ነበሩ።

የተፈራው አልቀረም፤ በንጋታው ጠዋት በከተማዋ ዳር ዳር የተቃውሞ ሰልፎች መታየት ጀመሩ። እየረፈደ ሲመጣ ወደ መሃል ከተማም መታየት ጀመሩ። በዕለቱ ከተማዋ ጸጥ ረጭ ብላ ዋለች። በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ደግሞ በዚሁ ግርግር ምክንያት ንጹሃን ተገደሉ፤ ንብረቶችም ወደሙ።

ከሃጫሉ ግድያ ጋር በተያያዘ እና ከግድያው በኋላ በተፈጠሩ ግርግሮች የተጠረጠሩ ፖለቲከኞ ታሰሩ። በአጠቃላይ ያ ክስተት ትልቅ አጀንዳ ሆኖ ቆየ። ክስተቱም እነሆ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይታወሳል። ወጣቱ ድምጻዊም በአጭር ተቀጠፈ። አድናቂዎቹና ወዳጆቹም ዓመቱን ሙሉ አዘኑ። እነሆ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳን 2ኛ የሙት ዓመት ምክንያት አድርገን በዚህ ሳምንት እናስታውሰዋለን።

ሃጫሉ ከእናቱ ወይዘሮ ጉደቱ ሆራ እና ከአባቱ ከአቶ ሁንዴሳ ቦንሳ በ1978 ዓ.ም በአምቦ ተወለደ። ከልጅነቱ ታሪክን መስማትና የመንገር ዝንባሌውንና ችሎታውን ጠንቅቀው ተረድተውት ስለነበር ወላጆቹ ያበረታቱት እንደነበር በተደጋጋሚ ቃለ ምልልስ ባደረገባቸው መድረኮች አስታውሷል።

የሃጫሉ የነፍስ ጥሪ ግን ወደ ሙዚቃው ሆነ። ገና በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ እያለ ሙዚቃዎችን መጫወት ጀመረ። በሙዚቃዎቹም የኦሮሞን ህዝብ ትግል የሚገልጹ መልዕክቶችን ያስተላልፋል። በዚህም ምክንያት ገና በ17 ዓመቱ ነበር የታሰረው።

መታሰሩ ከትግሉ ሊገታው ግን አልቻለም፤ እንዲያውም ይበልጥ በሥራው እንዲገፋበትና በሰዎች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እና ጭቆና የበለጠ እንዲታገል እንዳደረገው በተለያዩ ጊዜያት ተናግሯል።

ሃጫሉ በአፋን ኦሮሞ ተናጋሪው ሕዝብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅ የሆነለትን ‹‹ሰኚ ሞቲ›› የተሰኘውን አልበሙን አቀረበ። የዚህ የሙዚቃ ስብስብ አብዛኛዎቹ ግጥሞችና ዜማዎች ሃጫሉ በእስር ላይ እያለ የሰራቸው ነበሩ።

ሃጫሉ ተወዳጅ የሆኑ የአፋን ኦሮሞ የሙዚቃ ስልቶችን ከዘመናዊው ሙዚቃ ጋር በማጣመር በሚያቀርባቸው ሥራዎቹ የብዙዎችን ቀልብ ለመማረክ አስችሎታል። በአገሪቱ የሚገኙ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችም ሙዚቃዎቹን በተደጋጋሚ በማጫወታቸው በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ አድናቆትን ማግኘት ችሏል።



**የሃጫሉ የነፍስ ጥሪ ግን ወደ ሙዚቃው ሆነ:: ገና በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ እያለ ሙዚቃዎችን መጫወት ጀመረ:: በሙዚቃዎቹም የኦሮሞን ህዝብ ትግል የሚገልጹ መልዕክቶችን ያስተላልፋል:: በዚህም ምክንያት ገና በ17 ዓመቱ ነበር የታሰረው**

በእነዚህ የሙዚቃ ሥራዎቹ የሚታወቀው ሃጫሉ፤ ከአራት ዓመት በፊት የነበረውን ሥርዓት ለመቃወም በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የበለጠ ቀልብ ሳቢ ሆኖ መጣ። በለውጡ ዋዜማ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በተገኙበት በኦሮሚያ ሚዲያ ኔትዎርክ (OBN) ለመላው ዓለም በሚተላለፍ የቀጥታ ሥርጭት የብዙዎችን ቀልብ የሳበ፣ ዳሩ ግን የወቅቱን መንግሥት ቀልብ የገፈፈ ሥራውን አቀረበ።

ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ በሥራዎቹም ሆነ በመገናኛ ብዙኋን በሚያደርጋቸው ቃለ መጠይቆች፤ ሃጫሉ ከዘፈን ባሻገር ለኦሮሞ ሕዝብ መብትና ነፃነት በመታገሉ ለኦሮሞ ሕዝብ ዘፋኝ ብቻ ሳይሆን እንደ ታጋይ ይታያል።

አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ባለትዳር እና የሶስት ልጆች አባት ሲሆን፤ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ለብዙዎች ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ተገሏል። እነሆ ሥራዎቹና ታሪኩ ግን ሲታወስ ይኖራል።

### የደርግ ምሥረታ

ለሺህ ዘመናት የኖረውን ንጉሣዊ ሥርዓት፣ በተለይም ለግማሽ ክፍለ ዘመን የኖረውንና በኢትዮጵያ የመጨረሻ የሆነውን የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ንጉሣዊ ሥርዓት ያስወገደው ወታደራዊ ደርግ የተመሰረተው በዚህ ሳምንት ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም ነው።

የታሪክ ባለሙያዎች ደርግ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን ያስወገደበትን መንገድ ‹‹አዝጋሚው መፈንቅለ መንግሥት›› ይሉታል። ምክንያቱም አንድ ጊዜ አይደለም ያስወገዳቸው። የደርግ ምሥረታ ራሱ አንድ ጊዜ አይደለም። ሰኔ 21 ቀን በይፋ የተመሰረተበት ይሁን እንጂ ወታደሮቹ ሀሳቡን ከጠነሰሱትና የውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴውን ከጀመሩ ቆይተዋል።

ከታሪክ ባለሙያው ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983››፣ ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ‹‹ትግላችን›› መጽሐፎች እና ከተለያዩ ድረ ገጾች ባገኘናቸው መረጃዎች ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም የተመሰረተውን የደርግ መንግሥት ታሪክ እንዲህ እናስታውሳለን።

ደርግ የሚለው ቃል ከግዕዝ የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም ቡድን ወይንም ኮሚቴ ማለት ነው። ይህን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ለስርዓቱ መገለጫነት የተጠቀመው ግለሰብ ሻለቃ ናደው ዘካሪያስ ሲሆን ቀኑም፤ ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው የአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ መለዮ ለባሾች በየካቲት ወር ስለፈነዳው አብዮት ከሰኔ 19 ጀምሮ ውይይት ማካሄድ ጀመሩ። ደርግ በዝቅተኛ መኮንኖች (ከኮሎኔል ማዕረግ በታች) ከተመሰረተ በኋላ በዚያው ቀን ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም የደርግ ሊቀመንበር በመሆን ተመረጡ።

በ1953 ዓ.ም የተሞከረበትን መፈንቅለ መንግሥት ተከትሎ፤ የንጉሱ ሥርዓት የተለያዩ ጥገናዎችን ሲያደርግ ቢቆይም በ1966 ዓ.ም አብዮቱ ፈነዳ። አብዮቱን የጀመረው የወታደሩ መደብ ሲሆን፤ ነገሌ እና ሲዳሞ ላይ ሰፍሮ የነበረው የምድር ጦር ሠራዊት አዛዥ መኮንኖቻቸውን ሲያግቱ ይጀምራል። ጉዳዩ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በሚኖሩ የሰራዊቱ ክፍሎች ድጋፍን በማግኘቱ በወታደሩ መደብ ከመዛመቱም ባሻገር ወደ ተቀረው ዜጋም በመሰራጨት አብዮቱ ተቀጣጠለ። አሁንም የንጉሱ መንግሥት ብዙ ጥገናዎችን እያደረገ ነው። የዘውዱ መንግስት አብዮቱን ለማርገብ  የተለያዩ ለውጦችን አድርጓል። ለምሳሌ አክሊሉ ሃብተወልድን አንስቶ እንዳልካቸው መኮንንን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጓል።  ለወታደሩ ልዩ ደመወዝ ጭማሪ አድርጓል፤ ሊተገበር የነበረ የትምህርት ስርዓት ማሻሻያ ለውጥ በተነሳበት ተቃውሞ ምክንያት አስቁሟል። ሕገ መንግስት ለማሻሻል ሞክሯል። ይሄ ሁሉ ግን የወታደሩን አዝጋሚ መፈንቅለ መንግሥት ማስቀረት አልቻለም።

ሰኔ 21 ቀን በአራተኛ ክፍለ ጦር የተመሰረተው ደርግ የቀድሞ ባለሥልጣናትን ማሰር ጀመረ። ከሐምሌ 2 ቀን 1966 ዓ.ም ጀምሮ እስረኞቹ ጋዜጣና ራዲዮ እንዳያስገቡ ተከለከሉ። ጠያቂዎች እስረኞችን የሚጎበኙት በሳምንት አንድ ቀን ቅዳሜ ጧት ብቻ ነበር። ከሐምሌ 9 ቀን 1966 ዓ.ም በኋላ እሥረኞች ከነበሩበት የጎፋ ሠፈር ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ተዛወሩ።

እንዲህ እንዲህ እያለ የቆየው ደርግ፤ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ንጉሱን ገርስሶ መንግሥት መሆኑን በይፋ አወጀ። አሁን ደርግ የአገሪቱ መንግሥት ሆኗል። ንጉሠ ነገሥቱ ከሥልጣን መውረዳቸውን፣ ህገ መንግሥቱ መሻሩን፣ ፓርላማው መዘጋቱን አወጀ።

አላግባብ የበለጸጉ፣ ፍርድ ያጎደሉ፣ በአስተዳደር የበደሉ የተባሉ የቀድሞ ባለሥልጣናት ሁሉ በጦር ፍርድ ቤት የሚዳኙ መሆኑን ደርግ አዋጅ አስነገረ።  በዚሁ ዕለት የንጉሡ የልጅ ልጅ እና የባህር ኃይል አዛዥ የነበሩት ሪር አድሚራል እስክንድር ደስታ ተይዘው ከእሥረኞቹ ጋር ተቀላቀሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ ደርግ የታሳሪዎችን ቁጥር እያበዛው መጣ። በመጨረሻም፤ በታሪክ በጥቁር ቀለም የተጻፈውንና ደርግ እንደተወቀሰበት የሚኖረውን 60 የጦር መኮንኖችንና ባለሥልጣናትን የረሸነበት ድርጊት ተፈጸመ።

ደርግ በአራተኛ ክፍለ ጦር ተመስርቶ፣ መስከረም 2 መንግሥት መሆኑን አውጆ፤ አገር ባስተዳደረበት ዘመን በጨካኝነት የተገለጸውን ያህል፤ የአገር ዳር ድንበር በማስከበርና የውጭ ወራሪን አፈር ድሜ በማስበላት ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ታሪካዊ አዋጆችን አውጇል።

በየካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም  «የገጠር መሬት አዋጅ» እና ሐምሌ 19 ቀን 1967 ዓ.ም «የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ» በመባል የሚታወቁት ሁለት አዋጆች ተጠቃሽ ናቸው።


1966 ዓ.ም ተከትሎ የመጣው ለውጥ ቀደም ሲል የነበረውን የርስት ጉልት ግንኙነት በመሻር በመሬት ላይ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል። የደርግ ሥርዓት ይከተል በነበረው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም በመመራት ኢኮኖሚውን የሚመሩትን ዋና ዋና ነገሮች ከግል ባለቤትነት ወደ ሕዝብ ባለቤትነት አሸጋግሯል። የገጠር መሬትን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ በሚል አዋጅ ቁጥር 31/67 የሕዝብ ሀብት በሚል ታወጀ። አዋጁም መሬት አይሸጥም አይለወጥም የሚለውን ጥብቅ የሆነና የመሬት ጉዳይን ከሌሎች ንብረቶች የሚለየውን ገደብ ይዞ ብቅ ብሎ ነበር።

የገጠር መሬትን የሕዝብ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 31/67 አንቀጽ 5 አንድ የመሬት ተጠቃሚ በይዞታ የያዘውን መብት መሸጥ፣ መለወጥ፣ በስጦታ ማስተላለፍ፣ ማስያዝ፣ በወለድ አግድ ወይም በሌላ ሁኔታ ማስተላለፍ እንደማይችል ገደብ ያስቀምጣል። እነሆ ደርግ፤ ንጉሳዊ ሥርዓቱን ከመገርሰሱ ባሻገር በእነዚህና በሌሎች አዋጆች ይታወሳል።

# የዝነኞች ገጽ

# የአብዬ ዘርጋው ፈጣሪ - ሰለሞን አለሙ

**አቤል ገ/ኪዳን**



በ1952 ዓ.ም ታህሳስ 6 ቀን ከእናቱ ከወ/ሮ አምሳለ ዘለቀ እና ከአባቱ ከአቶ አለሙ ወልደማርያማ አዲስ አበባ እንጦጦ ቁስቋም ማርያማ አካባቢ ተወለደ:: የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን እቴጌ ጣይቱ ብጡል አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀቀ:: ከዚያ በኋላ ወደ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በመግባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቀቀ:: የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በአስመራ ዩኒቨርሲቲ ተከታትሏል:: የሰለሞን የኪነ ጥበብ ህይወት ግን የጀመረው ገና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለ በትምህርት ቤት በሚያቀርባቸው መነባንቦች እና ድርሰቶች ነበር::

ከዚያም በኋላ ወደ አስመራ ክፍለ አገር መሄዱ ለኪነ ጥበብ ህይወቱ ትልቅ እመርታ ሆነ:: በወቅቱ አስመራ ከፍተኛ የፖለቲካ ነውጥ የምታስተናግድ ከተማ የነበረች ቢሆንም በዚያ ነውጥ መሀልም ሆኖ ትልልቅ ስራዎችን መስራት ችሏል:: ከሰራቸው ስራዎች መካከል ደደቢ ወላንሳ፤ ብእሬ፤ እምቧሶራ፤ ሰው ማለት ቀይ ባህር እና መሰል ስራዎቹ ተጠቃሽ ናቸው::

ሰለሞን ህይወቱን በሙሉ የተለከፈበትን የኪነ ጥበብ ስራ የሰራው ግን ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ እነ ድርብ ወርቅ ሰይፉ፤ ሰራዊት ፍቅሬ እና መሰል ታላላቅ አርቲስቶችን ያፈራው አፍለኛው የቴአትር ክበብን ከመሰረተ በኋላ ነው:: የክበቡ መሪ እንዲሆን ከተመረጠ በኋላ ከምክትሉ ሰራዊት ፍቅሬ ጋር በመሆን አቅማቸው እና ተሰጥኦቸውን ለማስፈተሽ ወደ ቤተሰብ መምሪያ ሄዱ:: አቅማቸው ተፈትሾም የቤተሰብ መምሪያ የወጣቶች ፕሮጀክት ውስጥ እንዲሳተፉ እድሉ ተሰጣቸው:: ዘመን ተሻጋሪ የሆኑላቸውን እና እስከዛሬ የሚሞገሱባቸውን ስራዎች መስራት የቻሉትም እዚያ ነው:: በተለይም የሰለሞን ብእር ቀለም መትፋትን አላቆም አለ:: ለቁጥር የሚያታክቱ ድርሰቶችም ተፈጠሩ:: በስራዎቻቸውም መላው ኢትዮጵያን አካለሉ::

ሰለሞን ኮሜዲን በመጻፍ ቀዳሚ የሌለው ሰው ነው ብንል ማጋነን አይሆንም:: ህይወቱ ከህዝብ ጋር የተሳሰረ በመሆኑም በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ሲነሳ ተቸግሮ አያውቅም:: የሱን ጽሁፍ ወደ ትወና ለመቀየር ደግሞ አፍለኛው ውስጥ የነበሩ በርካታ ወጣት ተዋንያን ዋነኛ ጉልበቶቹ ነበሩ:: ፍራሽ ሜዳ፤ ከዳንኪራ ጀርባ፤ የሁለት አለም ሰዎች፤ በድሉ፤ አዞሪት፤ እና መሰል ስራዎች በወቅቱ ሰለሞን እና የአፍለኛው አጋሮቹ በጋራ ሰርተዋቸው ቴአትር ቤቶች በተመልካች እንዲጨናነቁ ያደረጉ ነበሩ:: ሳንካ እና ከል ጻዳል ደግሞ የሬድዮ አድማጩን ጆሮ ተቆጣጥረው ነበር:: ከነዚህ በኋላ ነበር ታሪካዊው ሽምጋይ የሬድዮ ድራማ የተሰራው:: አብዬ ዘርጋው በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በሬድዮ ድራማ ፍቅር ይጥሉ ዘንድ በሰለሞን ብእር በአፍለኛ ቡድን ትወና ተከሰቱ::

በአብዬ ዘርጋው የእሁድ ጠዋት ተከታታይ ድራማ ላይ ደራሲው ሰለሞን በድራማው ማጠናቀቂያ ታሪክ ላይ ዋናውን ካራክተር አብዬ ዘርጋውን እንዲሞቱ በማድረጉ በርካታ የድራማው አድማጮች በጣም ተቆጥተው ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል:: ያን ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ በመሄድ በሩ ላይ ‹‹አብዬ ዘርጋውን ደራሲው ከሞት ያስነሳልን›› በማለት በከፍተኛ ድምፅ በመጮህና በሬዲዮ ጣቢያው ስልክ እና ፖስታም በቁጣ በርካታ አድማጮች መልዕክት በማስተላለፍቸው ‹ተጠናቋል› የተባለውን ድራማ ጠቢቡ ሰለሞን ለአድማጮቹ ባለው ክብር የተነሳ በሚያስገርም ጥበባዊ ለዛ እና ጨዋነት አስመስክሯል:: ጎርፍ ወስዷቸው ሞተዋል ያላቸውን አብዬ ዘርጋውን ከወንዝ ዳር እንደተገኙ አድርጎ ከሞት አንስቶ አድማጮች በድጋሚ በድራማው እንዲዝናኑ ያደረገ ታላቅ ደራሲ ነው::

ሰለሞን እውነተኛ ደራሲ ነው:: ከመጻፍ ውጭ ሌላ የሚያስደስተው ነገር የለም:: በ80ዎቹ እና በ90ዎቹ ወደ ኢትዮጵያ የቴአትር ሰው በሙሉ ከሰለሞን ጋር ያልሰራ አይገኝም:: ሰለሞን አለሙ በአብዬ ዘርጋው ገኖ ይታወቅ እንጂ ከ500 በላይ ድራማዎችን መጻፉ ተመስክሮለታል:: ሰለሞን የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነበር::

**ዜና እረፍቱ ከተሰማ በኋላ ብዙ ወዳጆቹ ሀዘናቸውን የገለጹ ሲሆን የጥቂቶቹ እነሆ፡-**

"1970ዎቹ መጨረሻ ኤርትራ ክፍለ አገር የዱቄት ፋብሪካ ሠራተኛ ሆኖ በሄደበት ወቅት "አታ ግደፈኒ"፥ "አማን" የሚሉ ግጥሞችን በማቅረብ ይታወቃል። በዚያን ጊዜ ከሁለቱም ወገኖች ይፈለግ እንደነበረ አጫውቶኛል:: የተዋወቅሁት 1977 ዓ.ም ሸሮሜዳ አቶ ጃለታ ጃፈሮ ቤት ነው:: ከልጆቻቸው ጋር አብሮ አደግ ነው:: አብዬ ዘርጋውን እና ሌሎች ቀደምት ሥራዎቹን ይፅፍ የነበረው እዚህ ነበር:: ደደብዋ ወላንሣ የሚል ግጥሙንም 1980 ዎቹ መጀመሪያ ላይ ራስ ትያትር ሲያቀርብ አስታውሳለሁ።

**ወንድሜ ሠለሞን አለሙ ነፍስ ይማር! (ዶ/ር ሰለሞን ዓሊ- የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ፕሬዚዳንት)**

"ሰለሞን ሕይወቱን ለኪነ ጥበብ አሳልፎ የሰጠ፣ ዘመኑን በሚገባ ሰርቶበት፣ ሺሖችን ያፈራ፣ ሚሊዮኖች በሬዲዮ ድራማ ፍቅር እንዲወድቁ ምክንያት የሆነ አርቲስት! አገሩን፣ ወገኑን፣ ሕይወት ራሱን ጠንቅቆ የተረዳ ደራሲ ተዋናይ እና ገጣሚ ነበር::

**(ደራሲ ዳንኤል ወርቁ) ይህ ሰው ሐገሩን የሚወድ፣ ስራሱ ሃሳብና እምነት የታመነ ብእረኛ ነው::**

ለእውነት፣ ለፍቅር፣ ለፍትህና ለሰላም የላቀ ቦታ አለው:: ልበስሱ ነው:: ህይወቱን ሙሉ ለሚወደውና ለሚያከብረው ሙያ እየሰጠ የነበረ ሰው ነው:: ሰለሞን አለሙ ይባላል:: ደራሲ፣ አዘጋጅና ተዋናይ ነው:: ብዙዎች በተለምዶ "አብዬ ዘርጋው " እያሉ በሚጠሩት "ሽምጋይ" በተሰኘው ተከታታይ የሬዲዮ ድራማ ያውቁታል:: የራሱ የአፃፃፍ ይትበሃል (style) ያለው ፀሐፊ ነው:: በሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት ላይ አተኩሮ የሚፅፍ ታላቅና ጠንካራ ፀሐፊ ነው::

ሰለሞን ለሰናይ ምግባርና ለስነምግባር የቆመ ነው:: ለራሱ ሃሳብና እምነት የታመነ ብእረኛ ነው:: የእኩይ ድርጊቶች ጠላት ነው:: እውነት ብቻ ናት የብዕሩ ማዕከል:: ህይወቱ እውነት ናት:: ብእሩም ከህይወቱ የሚቀዳ ነው:: ሰለሞን በስራዎቹ ማህበራዊ ሃያሲ ደራሲ ነው ማለት እችላለሁ:: በርካታ በህዝብ ክብርና ፍቅርን ያጎናጸፉ የጥበብ ስራዎች አሉት::

በሐምሌ 1983 ዓ.ም በቤተሰብ መምሪያ የተገናኙት ሰለሞን እለሙ፣ ሠራዊት ፍቅሬ፣ አዜብ ወርቁ፣ ድርብወርቅ ሰይፉ፣ ፍሬህይወት መለሰ ሆነው በጋራ በከፈቱት "አፍለኛው" በተሰኘው የትያትር ቡድን ውስጥ ሰለሞን በጻፋቸው በርካታ ድርሰቶች አማካኝነት ብዙ ሰርተዋል::

ሰለሞን አለሙ 500 የሬዲዮ ድራማዎችን ፅፎአል:: እንደዛሬው ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች በሌሉበት ዘመን 13 ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎችን ፅፎ አዘጋጅቷል:: እንዲሁም 6 ትያትሮችን ጽፎ አዘጋጅቷል፣ ተውኗል:: በሌሎች ፀሐፊያን በተሰሩ የቴሌቪዥን ድራማዎችና ቲአትሮች ላይም ተውኗል::

ሰለሞን በርካታ መነባንቦችንም ለመድረክ አብቅቷል:: በተለይ በእሁድ ረፋድ ላይ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ለ70 ሳምንት ሲተላለፍ የቆየውና በመላው ኢትዮጵያን ዘንድ ተወዳጅ የነበረው " ሽምጋይ" ወይም (አብዬ ዘርጋው) የተሰኘው የሬዲዮ ድራማው ዛሬ ድረስ በብዙ ኢትዮጵያዊያን የሚታወስ ድራማ ነው:: ሠራዊት ፍቅሬ፣ አዜብ ወርቁ፣ ድርብወርቅ ሰይፉ፣ ፍሬህይወት መለሰ የዚህ ድራማ ፈርጥ (ጌጦች) ነበሩ:: ሰለሞን ትላንትም ዛሬም ይፅፋል::

(ጋዜጠኛ ይትባረክ ዋለልኝ) በእውቁ የኪነ ጥበብ ባለሙያ ጸሀፊ ተውኔት ሰለሞን አለሙ ህልፈተ ህይወት የተሰማኝን ሀዘን ስገልጽ ጥልቅ በሆነ የሀዘን ስሜት ነው:: ለቤተሰቡ፤ ለመላው የሙያው አድናቂዎች፤ እና ወዳጅ ዘመዶቹ በሙሉ መጽናናትን እየተመኘሁ ፈጣሪ ነፍሱን በአጸደ ገነት እንዲያሳርፈው ከልብ እመኛለሁ::

(ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን) ፀሐፊ ተውኔቱን፣ ደጉን፣ ሰው ወዳዱን፣ ተጫዋቹን ሰለሞን ዓለሙን ከእድሜዬ ከግማሽ በላዩን ያህል አውቀዋለሁ። በየጊዜው የምንደዋወልና በአካል የምንገናኝ አንሁን እንጂ ስንገናኝ ይበልጡን በእሱ ምክንያት ልብ የሚያሞቅ ወዳጅነት ይኖረናል። ሰለሞን መታመሙንና ወደመጨረሻ ላይም

**ሰለሞን ዛሬ የለም። ብሔድም ብቀርም አያየኝም። በሚያየኝ ሰዓት፣ ሰው በሚፈልግ ሰዓት፣ ደውሎ ሳይቀር ጠይቆኝ ባለ ሰዓት፣ ሰው በራበው ሰዓት፣ ወዳጅ በናፈቀው ሰዓት እኔ ከጎኑ አልተገኘሁም**

ያለ ኦክስጂን የማይንቀሳቀስ መሆኑን አውቃለሁ። ችግር ላይ እንደነበረም አውቃለሁ። ግን ዛሬ ነገ ስል አልጠየቅኩትም። በአቅሜ ያህል እንኳ አልደረስኩለትም። ብዙ ጊዜውን በህክምና ያሳለፈ እንደመሆኑ ገንዘብም ይቸግረው ነበር። አልደገፍኩትም። ገንዘብ አጥቼ ወይም ወዳጅነታችን የማያሰጥ ሆኖ ሳይሆን ቸልተኛ ሆኜ ነበር።

የግንኙነት ስፋቱን ያህል ሰዎች እየሄዱ አይጠይቁትም ስለነበር እናቱ " ደጉ ልጄ ምነው ወዳጅ ራቀው ? " ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። እኔም እንዲህ እንዲያስቡ ካደረጓቸው ሰዎች መሀል አንዱ ነኝ። ወዳጄ ወድቆ ቤት ሲውል ለራሴ አድልቼ የምችለውን ያህል እንኳ ጊዜ አልሰጠሁትም። " እንዴት ያደርግሀል ? " አላልኩትም። " ምን ይቸግርሀል ? " አላልኩትም። " እስቲ ይቺን ያዛት ለአንዳንድ ነገር እንኳ ትሆንሀለች " እንኳ አላልኩትም። " አይዞህ ሰሌ " አላልኩትም። ሰው እንዳለው፣ ወዳጅ እንዳለው እንዲሰማው አላደረኩትም። እንደውም አደባባይ ተወጥቶ ቢለመንለት ያስፈልገው ይሆን ነበር፤ ምናልባት። እሱ ከችግሩ ጋር ሲሆን እንዲደረግለት ፈልጎ ይሆን ነበር፤ ምናልባት። ይህን ሁሉ ማድረግ ሲገባኝ አላደረኩም። ታዲያ የእኔ ቀብሩ ላይ መገኘት ጥቅሙ ምንድነው ? ለማን ነው ? ለምንድነው ?

ሰለሞን ዛሬ የለም። ብሔድም ብቀርም አያየኝም። በሚያየኝ ሰዓት፣ ሰው በሚፈልግ ሰዓት፣ ደውሎ ሳይቀር ጠይቆኝ ባለ ሰዓት፣ ሰው በራበው ሰዓት፣ ወዳጅ በናፈቀው ሰዓት እኔ ከጎኑ አልተገኘሁም። ሁሉም ነገር ካለፈና ምንም ማድረግ በማልችል ሰዓት የሚያሳምም ፀፀት ተሰምቶኛል። ምንም ማድረግ አይቻልም። ይህን እንኳ ነግሬ ላገኘው አልችልም። ሄዷል። አምልጧል። በቃ ያ ደግ ሰው ሳጥን ውስጥ ገብቷል። አብቅቷል። ቀብሩ ላይ የመገኘት አንዳች የሞራል ብቃት የለኝም። ብገኝና ለታይታ ባለቅስ፣ ባለቀ ሰዓት ቤቱ ተገኝቼ ወዳጅ ብሆን ራሴን ይበልጥ እታዘበዋለሁ። እጠላዋለሁ። በሕይወት ላይ፣ በእውነት ላይ የዘሞትኩ ያህል ይሰማኛል። እኔ ድራማ እጽፋለሁ እንጂ ድራማ የሆነ ሕይወት አልኖርም። ወንድሜን ድጋሚ አልከደውም። የመጀመሪያው ይበቃዋል። ሰዎች ሰው በፈለገ ሰዓት ዛሬ ከጎኑ ተገኙ። ነገ በማንም እጅ የለችም። ነገ ፀፀት ነው ያለው:: ወንድሜ ሰለሞን ዓለሙ ደህና ሁን። ነፍስህ በሰላም ትረፍ። (**ጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ተክለ አረጋይ**)

ሰለሞን አለሙ የአቅሙን ያህል ሳይሆን፣ የማህበረሰቡን ፈቃድና የአገሩን አቅም ያህል ሰርቶ እንዳለፈ ይሰማኛል:: ከአመት በፊት ይመስለኛል የሆነ ቦታ ተገናኝተን በቁም ሰላምታችን መሀል፣ ይህንኑ አንስቼለት፣ ተቀምጠን ለመጨዋወት እንድንደዋወል ተነጋግረን ነበር:: . . . ይኸው ዛሬ አረፈ:: . . . ያልታደለ ማህበረሰብ በጎተራ ከተሰጣቸው (ከያዙለት) ላይ በእፍኙ እየቆነጠረ፣ ምንም ያልተሰጣቸውን (ያልያዙትን) ባዶ ቁና በአካፋ ይቧጥጣል:: . . . አቧራው የሚበዛው ለዛ ነው! (ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ)

# ዓለም አቀፍ

## በሊቢያ ተቃዋሚ ሰልፈኞች የአገሪቱን ፓርላማ ወረሩ

ተቃዋሚ ሰልፈኞች በምሥራቃዊቷ የሊቢያ ከተማ ቱብሩክ ውስጥ የሚገኘውን የአገሪቱን ፓርላማ ወረው ከፊል ሕንጻውን በእሳት ማቃጠላቸው ተዘገበ። በበይነ መረብ ላይ የተሰራጩ ምስሎች ከፓርላማው ሕንጻ ውጪ የተሰባሰቡ ተቃዋሚ ሰልፈኞች ጎማዎችን ሲያቃጥሉና ጥቁር ጭስ አካባቢውን ሲሸፍነው አሳይተዋል።

በተለያዩ የሊቢያ ከተሞችም የኤሌክትሪክ ኃይል መቋረጥን፣ የዋጋ ንረትን እና ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን በመቃወም ሰልፎች ተካሂደዋል። በሌላ ተቀናቃኝ ኃይል አስተዳደር ስር በምትገኘው በዋና ከተማዋ ትሪፖሊም ምርጫ እንዲደረግ የሚጠይቅ ሰልፍ ተደርጓል።

ጥቂያቸውም በሊቢያ ተቋማት ላይ ለውጥ መደረግ አለበት በሚሉትና የአገሪቱ ጊዜያዊ የአንድነት መንግሥትን በሚመሩት አብዱል ሃሚድ ቢባህ ድጋፍ አግኝቷል። ተቃውሞው የተከሰተው በተባበሩት መንግሥታት አማካይነት በአገሪቱ ምርጫ እንዲካሄድ ለማስቻል ጄኔቫ ውስጥ ተካሂዶ እምብዛም ውጤታማ ያልሆነው ንግግር ከተከናወነ ከአንድ ቀን በኋላ ነው።

ሊቢያ ለረዥም ዓመታት የመሯት ኮሎኔል ሞአማር ጋዳፊ በሰሜን አትላንቲክ ጦር ኃይሎች ድጋፍ ከአሥር ዓመት በፊት ከሥልጣን ተወግድው ከተገደሉ በኋላ በቀውስ ውስጥ ትገኛለች።

በነዳጅ ሃብት የበለጸገችው ሊቢያ ግጭት ውስጥ ከመግባቷ በፊት ዜጎቿ ነጻ ሕክምናን እና ትምህርትን በማግኘት በአፍሪካ በከፍተኛው የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኙ ነበር። በአሁኑ ወቅት መንግሥታዊ ሥርዓቷ በእርስ በርስ ጦርነትና ክፍፍል ምክንያት በመንኮታኮቱ ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት ወደ አውሮፓ ለመሻገር ለሚፈልጉ ስደተኞች ዋነኛ መተላለፊያ መስመር ናት።

ለብልጽግናዋ ወሳኝ የነበረው ሰላሟ በመናጋቱ በዋና ከተማዋ ትሪፖሊ ውስጥ ሳይቀር ተቀናቃኝ ኃይሎች የበላይነትን ለመያዝ ተደጋጋሚ ውጊያ እንደሚያደርጉ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።



## 3.2 ቢሊዮን ዶላር አጭበርብራ የተሰወረችው ”የክሪፕቶ ንግሥት‘ በኤፍቢአይ እየተፈለገች ነው

ሩጃ ኢግናቶቫ ወይም “የጠፋችው የክሪፕቶ ንግሥት” በአሜሪካ የፌደራል ምርመራ ቢሮ ኤፍቢአይ በጥብቅ ከሚፈለጉ 10 ሰዎች ውስጥ ተካታለች። የቡልጋሪያ ዜግነት ያላት ግለሰቧ ‘ዋን ኮይን’ በሚሰኝ የክሪፕቶ ከረንሲ አይነት ማጭበርበር ውስጥ ተሳትፎ አላት የሚል ውንጀላ ይቀርብባታል።

ተጠርጣሪዋ ከተለያዩ ሰዎች 3.2 ቢሊዮን ዶላር ግምት ያለው ገንዘብ አጭበርብራ መሰወሯን የአሜሪካ ፌዴራል መርማሪዎች ይገልጻሉ። ከአውሮፓውያኑ 2017 ወዲህ የገባችበት ያልታወቀው ሩጃ ኢግናቶቫ የእስር ማዘዣ የወጣባት ሲሆን መርማሪዎች ክትትል እያደረጉባት ነው።

ግለሰቧ ‘ዋን ኮይን’ የተባለው እና እንደ አውሮፓውያኑ በ2014 የተጀመረው የዲጂታል ገንዘብ/ክሪፕቶከረንሲ ውስጥ ተሳትፎ እንዳላት የምትጠረጠር ሲሆን ገዢዎች ብዙ ሰዎችን ባመጡ ቁጥር ብዙ ኮሚሽን እንዲያገኙ አደርጋለው የሚል ነው።

ሆኖም ኤፍቢአይ ‘ዋን ኮይን’ ረብ የለሽ እና እንደሌሎች የክሪፕቶከረንሲ ዓይነቶች አስተማማኝ የደኅንነት መጠበቂያ ኖሮት የማያውቅ ነው ብሎታል። የፌዴራል ጠበቆች እንደሚያቀርቡት ክስ ከሆነ ‘ዋን ኮይን’ አጭበርባሪ ሲሆን፣ ስሙን ቀይሮ በክሪፕቶከረንሲ መልክ ብቅ ያለ ነው።

ተጠርጣሪዋ “ክሪፕቶ ከረንሲ ሲጀመር የነበሩ እና በስፋት የሚወሩ መላምቶችን በሚገባ በመጠቀም ለማጭበርበር የሚበጃትን ትክክለኛ ሰዓት መርጣለች” ሲሉ ዳሚያን ዊሊያምስ የተባሉ ዐቃቢ ሕግ ተናግረዋል። በዚህም ሳቢያ በአሁኑ ወቅት የት እንዳለች የማትታወቀዋን ግለሰብ ኤፍቢአይ በብርቱ ከሚፈለጉ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ማካተቱን የገለጸ ሲሆን፣ ይህም ተጠርጣሪዋን በማፈላለጉ ሂደት ዜጎች እንዲረዱት ያግዛል ተብሏል።

ታዲያ እንደ አውሮፓውያኑ በ2019 ስምንት ክሶች የቀረቡበታን ኢግናቶቫ ለሚጠቁም የ100 ሺህ ዶላር ሽልማት እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል። ሴትየዋ በኤፍቢአይ በጥብቅ ከሚፈለጉ 10 ሰዎች ውስጥ የተካተተች ብቸኛ ሴት ናት። በዚህ ዝርዝር ውስጥ መካተቷ ደግሞ የመያዝ ዕድሏን ከፍ ያደርገዋል ተብሏል።

የግለሰቧን ጉዳይ ሲከታተሉ የነበሩት አንድ መርማሪ ተጠርጣሪዋ ከሕግ ለመሰወር 500 ሚሊዮን ዶላር ማውጣቷን የገለጹ ሲሆን ይህም ፍለጋውን እጅግ አስቸጋሪ እንዳደረገው ጠቅሰዋል። ራሷን የመደበቅ እና ሐሰተኛ ማንነት የመጠቀም ከፍተኛ ብቃት እንዳላት የተናገሩት መርማሪው በህይወት ላትኖርም ትችላለች የሚል ግምት አላቸው።



ሩጃ ኢግናቶቫ

“የጠፋችው የክሪፕቶ ንግሥት” ለመጨረሻ ጊዜ የታየችው እንደ አውሮፓውያኑ በ2017 ከቡልጋሪያ ወደ ግሪክ ባቀናችበት ጊዜ ሲሆን ከዚያ ጊዜ በኋላ ግን ደብዛዋ መጥፋቱን ቢቢሲ ዘግቧል።


### ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 05 የቤት ቁጥር 649 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0007069385 በቀለ ወ/ሰንበት ታደሰ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ጉለሌ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 001 እስከ 500 ያልተሰራበት እና የእጅ በእጅ ሽያጭ ተርን ኦቨር ታክስ /ቲኦቲ/ ከቁጥር 251 እስከ 1000 ያልተሰራበት እንዲሁም የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከ01 እስከ 250 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ጉለሌ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም በቀለ ወ/ሰንበት ታደሰ**

### ማስታወቂያ

ቫይብራኒየም ሪሶርስስ ፋውንዴሽን የተባለ አገር በቀል ድርጅት ከዚህ በፊት ያልነበረ ሲሆን ከዚህ በታች በተቀመጠው አርማ የሚጠቀም መሆኑን እያሳወቅን

VIBRANIUM RESOURCES FOUNDATION

ተቃዋሚ ካለ እስከ ሐምሌ 02/2014 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ሕብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 403 ድረስ ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

### ማስታወቂያ

አዲስ ፈና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላ/የተ/የህብረት ሥራ ማህበር በ10/10/2014 ዓ.ም በደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በ30/8/2014ዓ.ም ባደረገው በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ውሳኔ አዲስ ፈና የገንዘብ ቁጠባና ኃ/የተ የህብረት ሥራ ማህበር ለመዋሀድ ወስነዋል፡፡ ስለዚህ ቅሬታ ወይም ተቃውሞ አለኝ የሚል አካል ካለ በ30 ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርጉ ተጠቅሶ በጋዜጣ ላይ እንዲወጣላቸው ጠይቀዋል፡፡

**አዲስ ፈና የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃላ/የተ/የህብረት ሥራ ማህበር**

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም፡- መሀመድ ሙዘሚል ሬድዋን<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 1893, ጉለሌ, አዲስ አበባ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር፡- LTM/11754/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 02/06/2014 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡-<br>Gallery | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 7 እና 11 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የልብስ ማጠቢያ(ምድብ 7) እና ፊሪጅ<br>(ምድብ 11) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN Vol. LXXXI No. 296- 26/10/2014 (3/7/2022)**

### ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ ልዩ የገንዘብ እና የእገዛ ተቋም ሰንዳፋ ቅርንጫፍ እና በተከሳሾች በእነ 1. ዘቡ ጌቱ 2. እሙዬ መኮንን ገበየሁ 3. ዝናሽ ፈለቀ ዘርፉ መካከል ያለውን የፍትሐብሄር ክርክር አስመልክቶ ዘቡ ጌቱ እና እሙዬ መኮንን ገበየሁ ተብለው ለሚጠሩት መከሰሳቸውን አውቀው በችሎት ቀርበው እንዲከራከሩ ጥሪ አድርጋችሁ ውጤቱን በቀጠሮ ቀን 01/11/2014 ዓ.ም በ04፡00 ሰአት ላይ ሪፖርቱን ለችሎቱ እንድታቀርቡ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

1ኛ አቶ ቤካ ሀይሉ 2ኛ. ወ/ሮ ሜሮን ታደሰ - ሁለት ሰዎች በከሳሽ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና በተከሳሽ 1ኛ አቶ ቤካ ሀይሉ 2ኛ. ወ/ሮ ሜሮን ታደሰ ሁለት ሰዎች መካከል ያለውን የፍታብሔር ክርክር አስመልክቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መከሰስዎን አውቀው በ13/11/2014 ዓ.ም ከጠዋት 4:30 ቀርበው እንዲከራከሩ፣ ያልቀረቡ ከሆነ በሌሉበት ክርክሩ የሚካሄድ መሆኑን አውቀው ቀርበው እንዲከራከሩ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍታብሔር ችሎት**




# ክረምት በእነ ሕንደኬ እና ኀርየነ-መስቀል ቤት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

እንደምን አላችሁ ልጆች፣ ሰላም ናችሁ? ሳምንቱ እንዴት አለፈ፣ ጥሩ ነበር አይደል? የፈተና ውጤታቸችሁስ ምን ይመስል ነበር? መቼም የፈተና ውጤታችን በጣም ጥሩ ነው እንደምትሉኝ አምናለሁ:: ምክንያቱም ጎበዝ የሆነ ተማሪ በምንም መልኩ በፈተና አይወድቅም:: በዚያ ላይ እናንተ ዛሬ የተማራችሁትን ዛሬውኑ የምታነቡ ልጆች ስለሆናችሁ በጥሩ ውጤት ከክፍል ወደ ክፍል እንደተዛወራችሁ ይሰማኛል::

ንባብ የሚወድ ልጅ የዛሬውን ፈተና ብቻ ሳይሆን የነገውን ተስፋውን ጭምር የሚያቃና ነው:: እናም እናንተ ይህንን እንደምታደርጉ እርግጠኛ ነኝ። ደግሞ አሁን ወቅቱ ክረምት ስለሆነ የበለጠ የምታነቡበት ጊዜ ይኖራችኋልና በደንብ ተጠቀሙበት:: ብዙ እረፍት ስታገኙ መዘናጋት የለባችሁም:: ጎበዞች ከሆናችሁ ለአገራችሁም ለቤተሰባችሁም ኩራት ትሆናላችሁ። ልጆች ለዛሬው ይዘንላችሁ የመጣነው በጣም የምትወዱትን የእረፍት ጊዜ ይመለከታል:: ልጆች እንዴት ይህንን የእረፍት ጊዜያቸውን ሊያሳልፉ ይገባል በሚል ተሞክሯቸውን ያካፈሉንን ልጆች ነውም የምናቀርብላችሁ::

እነርሱ የሚያደርጉትን ነገር በደንብ ነግረውናል:: እናንተም ማድረግ ያለባችሁንም እንዲሁ በምክር መልኩ አስረድተውናል:: ልጆቹን ከማስተዋወቃችን በፊት ግን ስለ ክረምት ምንነት ጥቂት እንበላችሁ:: ልጆች ለመሆኑ ክረምት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? የምታውቁ ጎበዞች የማታውቁ ደግሞ እኔ ጥቂት ነገር ከተለያዩ መረጃዎች ያገኘሁትን አብነት በማድረግ ልንገራችሁ::

ክረምት ማለት ስርወ ቃሉ ከርም፤ ከረመ የሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን፤ ትርጉሙም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጎድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። በተጨማሪም የዝናብ፣ የአዝርዕትና የዕጽዋት መለምለምና ምድር በአረንጓዴ



የምታሸበርቅበት ወቅት እንደማለት ነው:: በመሆኑም በአገራችን ብዙው የግብርና ሥራ የሚካሄደው በዚህ ጊዜ ነው::

የክረምት ወቅት የሚባለው ከሰኔ 26 ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም 25 ቀን ድረስ ነው። ይህንን ወቅት ደግሞ ብዙ ሰዎች በተለያየ አስተምሮ ይገልጹታል፤ ይዘምሩለታልም:: አንዱ ኢትዮጵያዊው የቅኔና የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ ሲሆን፤ በድጓው ‹‹ ‹ደምፀ እገሪሁ ለዝናብ ሶቦ ይዘንብ ዝናብ ይትፌስሑ ነዳያን ደምፀ እገሪሁ ለዝናብ ሶበ ይዘንብ ዝናብ ይፀግቡ ርሁባን› የዝናም ድምፅ ተሰማ፤ ዝናም በዘነመ ጊዜ ችግረኞች ይደሰታሉ፤ ረሀብተኞችም ይጠግባሉ::›› በማለት ይዘምረዋል::

ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙሩ ‹‹ ሰማዮችን በደመና ይሸፍናል፤ ለምድርም ዝናምን ያዘጋጃልና፤ ሣርን በተራሮች ላይ ያበቅላል፤ ለምለሙንም ለሰው ልጆች ጥቅም›› በማለት በዝማሬው ይሰብካል:: እናም ልጆች ክረምት ለእናንተ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰላም የሚሰጥ ወቅት ነው:: ስለዚህም በብዙ መልኩ መጠቀም ይኖርባችኋል:: ያነጋገርኳቸው ልጆችም በብዙ ነገር እንደሚጠቀሙበትና ገና ትምህርት ሳይዘጋ እቅድ ይዘው እየተጠባበቁት እንደነበር ነግረውናል::

መጀመሪያ ያነጋገርኳት ልጅ ሕንደኬ ሙሉቀን ትባላለች:: የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን እስኮ አካባቢ በሚገኝ ሚረር አካዳሚ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ትማራለች:: በትምህርቷ በጣም ጎበዝ ስትሆን በበጋው ወቅት ትምህርቷን በአግባቡ ተከታትላና አንብባ ውጤታማ ሆናለች:: በዚህም የደረጃ ተማሪ በመሆን ተሸልማለች:: ክረምትም ቢሆን የቀጣዩን ክፍል በከፍተኛ ውጤት ለማለፍ ቀድማ እንደምትዘጋጅበትና መፀሐፍቶችን በእጇ እንዳስገባች ነግራኛለች::

ልጆች ማንኛውም ተማሪ ዝም ብሎ ጎበዝ አይሆንም:: ባለው ጊዜ እውቀት ሊያስጨብጠው የሚያስችለውን ተግባር መከወን አለበት የምትለው ህንደኬ፤ በተለይ ክረምትን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል:: ትምህርቱ ያልደረስንበት ቢሆንም የከበደንን ከሚያውቁት ወላጆቻችን ጠይቀን እየተረዳን ማንበብ አለብንም ባይ ናት:: የልጆች አንዱ የክረምት እቅዳቸው ይህ መሆን እንዳለበትም ትመክራለች::

ልጆች እንደኬ ሌላው ያነሳችው ነገር ክረምት ከባድ ዝናብ የሚጥልበት ወቅት በመሆኑ ልጆች ከቤታቸው ሲወጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ነው:: እንደውም ከወላጆቻቸው ፈቃድ ውጪ የትም መሄድ የለባቸውም:: ብቻቸውንም ባይወጡ መልካም ነውም ትላለች::

እንደኬ መሆን የምትፈልገው ሞዴሊስትና ዶክተር መሆን ነው:: ዶክተርነትን የመረጠችበት ምክንያት የታመሙ ሰዎችን ማከም ስለምትፈልግ ነው:: ስለዚህም ለዚያ የሚያበቃትን ዝግጅት ከአሁን ጀምራ እየከወነችም ትገኛለች:: ሳይንስ ትምህርቶችን አጥብቃ የመውደዷም ምስጢር ይህ እንደሆነ ታስረዳለች:: ሌላው የነገረችን ነገር በክረምት ማድረግ ከሚያስደስታት ውስጥ አንዱ ጨዋታ ነው:: ከጥናት በኋላ እረፍት እንደሚያስፈልጋት በደንብ ታውቃለችም የምትወዳቸውን ጨዋታዎች በሙሉ ለመጫወት ትሞክራለች:: ልጆችም ጥናታቸውን ሲጨርሱ ራሳቸውን ዘና ማድረግ እንዳለባቸው ትመክራለች:: ነገር ግን ይህንን ሲያደርጉ ለእነርሱ የሚመጥን ጨዋታ መምረጥ እንዳለባቸው ታሳስባለች::

ወንድሟ ኀርየነ-መስቀል ሙሉቀንም እንዲሁ የእርሷ አይነት ባህሪ አለው:: ይሁን እንጂ ከእርሷ በአንድ ነገር ይለያል:: ይህም በጣም ጎበዝ ተማሪ በመሆኑ በማጠቃለያው ፈተና አንድ ክፍል ከፍ ብሎ ያልተማረውን ተፈትኖ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በመድፈን እና ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ያለፈ ልጅ ነው:: መምህሮቹ በጣም ይገረሙበታልም:: ምክንያቱም ሁሌም ትምህርቱን በሙሉ ይደፍነዋል:: ኤክስ የሚባል ነገር አያውቅም:: እንደውም አንዳንዴ መምህራንን ጭምር በእርሱ እድሜ ደረጃ የማይጠየቁ ጥያቄዎችን እያነሳ ያስገርማቸዋል::

ኀርየነ-መስቀል በቤት ውስጥ ጭምር የተጠየቀውን ቀድሞ የሚመልስና የሚያደርግ ልጅ ነው:: እናም ክረምትን ማሳለፍ የሚፈልገው በማንበብና የክረምት ትምህርት በመማር እንደሆነ ነግሮናል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እረፍት ሲኖረው ቤተሰቡን በማገዝ ማሳለፍ ይፈልጋል:: መሆን የሚፈልገው እንደ እህቱ ዶክተር ቢሆንም የመጀመሪያ ምርጫው ግን ፖሊስነት ነው:: ይህንን የሚፈልገው ደግሞ ሌቦች በአገራችን እንዳይኖሩ ለማድረግና ሕግን ለማስከበር ስለሚፈልግ ነው:: እንዴት ነው ልጆች፤ ጎበዝ አይደለም? እርግጠኛ ነኝ የሁለቱንም ልጆች ታሪክ ወዳችሁታል:: ምክራቸውንም እንደምትሰሙ አስባለሁ:: ምክራቸውን ስሙ እያልን ለዛሬ አበቃን:: መልካም የክረምት ወራት ይሁንላችሁ !!

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግና ቻምፒዮኖቹ

**ቦጋለ አበበ**

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ትልቁ የውድድር መድረክ ‹‹ፕሪሚየር ሊግ›› በሚል ስያሜ ወጥ በሆነ መንገድ መካሄድ የጀመረው ከ1990 ጀምሮ ነው:: ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ጉዞውም የተለያዩ ቻምፒዮኖችንና መሰረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ለውጦችን አስተናግዷል። የዘንድሮውን ጨምሮም 24 ዋንጫዎችን የተለያዩ ክለቦች ማንሳት ችለዋል:: ከነዚህ 24 ዋንጫዎችም ቅዱስ ጊዮርጊስ የዘንድሮውን ጨምሮ 15ቱን በመሰብሰብ ሃያል ከመሆኑ ባሻገር ፍፁም ሊባል የሚችል የበላይነት አለው። ቀሪዎቹን 9 ዋንጫዎች 5 የተለያዩ ክለቦች ወስደዋል።

የመጀመሪያውን ዋንጫ በማንሳት ስሙን በታሪክ ማህደር ላይ ያሰፈረው ከሊጉ ወርዶ ከዓመታ በኋላ ዘንድሮ መመለሱን ያረጋገጠው የቀድሞው መብራት ኃይል የአሁኑ ኢትዮ ኤሌክትሪክ ነው። መብራት ኃይል ያኔ ከ24 ዓመት በፊት የመጀመሪያውን ዋንጫ ሲያነሳ 32 ነጥቦችን ሰብስቦ ነበር። ይህን ነጥብ የሰበሰበውም ስምንት ግቦችን ብቻ በማስቆጠር ነበር።

ባለፈው ሐሙስ 15ኛ ዋንጫውን መሳም የቻለው ቅዱስ ጊዮርጊስ ለመጀመሪያ ጊዜ ዋንጫ የቀመሰው በ1991 ነው:: 10 ክለቦች ብቻ በተሳተፉበት ውድድር ነበር:: በቀጣይ ዓመትም ፈረሰኞቹ ዋንጫውን የነጠቃቸው አልነበረም። የክለቦች ቁጥርም በዚያ ወቅት ወደ 12 ከፍ ብሎ ነበር። 1993 ዓ.ም መብራት ኃይል ከሁለት ዓመት በኋላ ዳግም ወደ ንግስና የተመለሰበት ነው:: መብራት ኃይል የነዚህን ዓመት ዋንጫ በማንሳት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቀጥሎ ከአንድ ጊዜ በላይ ቻምፒዮን የሆነ ብቸኛው የአዲስ አበባ ክለብ ነበር:: ከዚህ ድሉ በኋላ ግን ወደ ዋንጫ አልተመለሰም። በዚያ ወቅት የተሳታፊ ክለቦች ቁጥርም ወደ 14 ከፍ ብሎ ነበር። 1994 የውድድር ዓመት ፈረሰኞቹ ዳግም ወደ ኃያልነት



ፈረሰኞቹ 15 ጊዜ የፕሪሚየርሊጉን ዋንጫ በማንሳት ከሌሎች ክለቦች ጋር ያላቸውን ልዩነት የበለጠ አስፍተዋል፣

የተመለሱበት ሆኖ ይታወሳል:: ፈረሰኞቹ ለ3 ጊዜ ቻምፒዮን ሲሆኑ፣ በቀጣዩ ዓመትም ለ4ተኛ ጊዜ በሊጉ ነግሰውበታል::

1996 ዓ.ም በፕሪሚየር ሊጉ ታሪክ አዲስ ክስተት ይዞ የመጣ ዓመት ነበር። ሐዋሳ ከነማ ለመጀመሪያ ጊዜ የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ ያነሳ የመጀመሪያው የክልል ክለብ ሆነ። ቢያንስ በ2 ዓመት አንድ ጊዜ መንገስ የለመዱት ፈራሰኞቹ ከሁለት ተከታታይ ድሎቻቸው በኋላ ዳግም ወደ ቻምፒዮናነት የተመለሱት በ1997 ነበር። ይህም 5ኛ ድላቸው ሆኖ ሲመዘገብ ቀጣዩን ዓመትም ከቻምፒዮንነት ያቆማቸው አልነበረም:: 1998 ውድድር ዓመት ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ በ14 ክለቦች መካከል ሲካሄድ የቆየው ፕሪሚየር ሊግ ወደ 15 ከፍ ብሎም ነበር።

ሐዋሳ ከነማ አንድ ጊዜ ብቻ ዋንጫውን አንስቶ አልቀረም፣ ከሁለት ዓመት በኋላ ተመልሶ በ1999 ዓ.ም ሌላ ጣፋጭ ድል አጣጥሟል። በዚህ ዓመትም የተሳታፊ ክለቦች ቁጥር ወደ 16 ከፍ ብሎ የነበረ ቢሆንም 10 ክለቦች ፕሪሚየር ሊጉን አቋርጠው በ6 ክለቦች ነበር ዓመቱ የተጠናቀቀው::

የኢትዮጵያ ሚሌኒየም 2000 ዓ.ም ላይ የፕሪሚየር ሊጉ ተሳታፊ ክለቦች ቁጥር ወደ 25 አሻቅቧል። የእዚህን ዓመት ዋንጫም ፈረሰኞቹ ከአንድ ዓመት ረፍት በኋላ ለ7 ጊዜ አንስተውታል። በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታትም ፈረሰኞቹን ከዙፋናቸው ያወረዳቸው ክለብ አልነበረም። የተሳታፊ ክለቦች ቁጥር ወደ 16 ዝቅ ባለበት 2001 ዓ.ም ፈረሰኞቹ ዋንጫውን ለ9 ጊዜ ስመውታል። ቀጣዩ 2002 ዓ.ም የተሳታፊዎች ቁጥር 18 ነበር። ፈረሰኞቹም 10ኛውን ዋንጫ ከፍ አድርገዋል። ለተከታታይ ሦስት ጊዜ በማንሳትም የመጀመሪያ ታሪካቸው ነው::

2003 ዓ.ም ፕሪሚየር ሊጉ ሌላ አዲስ ታሪክ ያየበት ወቅት ነው። የበርካታ ደጋፊዎች ባለቤት የሆነው ኢትዮጵያ ቡና በእዚህ የውድድር ዓመት ከ16 ክለቦች ጋር ተፎካክሮ ለበርካታ ደጋፊዎቹ ዋንጫ አበርክቷል። በቻምፒዮኖቹ የታሪክ ማህደርም ኢትዮጵያ ቡና መድገም ያልቻለውን ዋንጫ በአሁኑ የዋልያዎቹ አለቃ ውበቱ አባተ እየተመራ አዲስ ንጉስ ሆኖ ተመዝግቧል።

ፈረሰኞቹ በ2004 የውድድር ዓመት በቻምፒዮናነት ተመልሰዋል። 14 ክለቦች ቋሚ በሆነ መንገድ መሳተፍ በጀመሩበት የውድድር ዓመት ፈረሰኞቹ ወደ ዙፋናቸው የተመለሱት 59 ነጥቦችን በመሰብሰብ ነበር። ቀጣዩን ዓመት ግን ፈረሰኞቹ እንደተለመደው ድላቸውን መድገም ሳይችሉ ቀርተዋል። በእዚህም ለፕሪሚየር ሊጉ እንግዳ የሆነውና መሳተፍ ከጀመረ ገና አራት ዓመታትን ያስቆጠረው ደደቢት በኮከብ ግብ አግቢውና ኮከብ ተጫዋች ሆኖ በተመረጠው ጌታነህ ከበደ ፊት አውራሪነት የሊጉ አዲስ ቻምፒዮን ለመሆን በቃ። ይህም ታሪካቸው ፕሪሚየር ሊጉን ከፈረሰኞቹ ውጪ ያነሱ 4ኛው ክለብ አድርጓቸው ነበር። 2006 ለፈረሰኞቹ እንደተለመደው ከአንድ ዋንጫ በኋላ ወደ ቻምፒዮናነት የተመለሱበት ነው። ቀጣዩ ዓመትም ፈረሰኞቹ ሊጉ ገና ሁለት ጨዋታዎች እየቀሩት ለ12 ጊዜ መንገሳቸውን በጊዜ ያረጋገጡበት ሆኗል። የቡድኑ አምበል ደጉ ደበበም ከ12ቱ ዋንጫዎች 7ቱን አብሮ በማንሳት ከክለቡ ጋር አዲስ ታሪክ አኑሯል። በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት ፕሪሚየር ሊጉ ተሳታፊዎቹን ከ14 ወደ 16 ባሳደገባቸው ዓመታት ፈረሰኞቹ ብዙም ሳይቸገሩ ተከታታይ ዋንጫዎችን ማንሳት ችለዋል። በተከታታይ አራት ዓመታት ፈረሰኞቹ ቻምፒዮን በመሆን አዲስ ታሪክ በፃፉበት የውድድር ዓመት የፕሪሚየር ሊጉ ደረጃና ጥራት ከመውረዱ ባነሰ ጨዋታዎችም ለተመልካች እጅግ አሰልቺና ፉክክሩም ደብዛዛ ነበር።

ከነዚህ የውድድር ዓመታት በኋላ ግን ከ2010 ጀምሮ ፕሪሚየርሊጉ በአዳዲስ ቻምፒዮኖች አብዮት የተቃኘ ሆኗል:: ለሦስት የውድድር ዓመታትም የተለያዩ የክልል ክለቦች ወደ ቻምፒዮንነት ሊመጡ ችለዋል:: የያኔው ጅማ ከነማ የአሁኑ ጅማ አባጅፋር የጀመረውን የቻምፒዮንነት አብዮት መቐለ ከተማና ፋሲል ከነማ ተቀላቅለው ያለፉትን ሦስት ዋንጫዎች ማንሳት ችለዋል:: ፈረሰኞቹም ከነዚህ ዓመታት በኋላ ባለፈው አርብ 15ኛውን ዋንጫ በማንሳት ወደ ቻምፒዮንነት ተመልሰዋል::